

በ፲፩ኛው ምእት ዓመት ከብርና ከነሐስ የተሠራው በቅርቡ ታሪካዊ የሆነው መስቀል ።

# ትንሣኤ



ጸጋን የተመላሽ ድንግል ማርያም ሆይ ፡ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ።

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 23 ፲፱፻፷፩

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጐምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት

የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ

በወር አንድ ጊዜ

እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616

የመልእክት ሣ.ቁ. 3137

አዲስ አበባ


ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ........................ | ፩ |
| ደብዳቤዎች ........................ | ፪ |
| እውነት ያሸንፋል ........................ | ፫ |
| ምልዕተ ጸጋ ማርያም ........................ | ፬ |
| ክርስቲያናዊ ሕይወት ........................ | ፭ |
| ምን እንርዳዎ ? ........................ | ፮ |
| ይህን ያውቁ ኖሯል ? ........................ | ፱ |
| ቤ/ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ ........................ | ፲ |
| የሃይማኖት ዐምድ ........................ | ፲፪ |
| የኢትዮጵያ ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች ........................ | ፲፫ |
| ለቤተ ክርስቲያን ማሳተሚያ ድርጅቶች ........................ | ፲፭ |
| የጤና ዓምድ ........................ | ፲፯ |
| ሊቃውንቶቻችን ........................ | ፲፰ |
| ዜና ሀገረ ስብከት ........................ | ፲፱ |
| የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና ........................ | ፲፱ |
| የሴቶች ዐምድ ........................ | ፳ |
| አስተያየት ........................ | ፳፩ |
| ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች ........................ | ፳፪ |
| ከመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ........................ | ፳፬ |



የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ሦስተኛ ዓመት በዐለ ሢመት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓመተ ምሕረት በጸሎትና በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐት ይከበራል



www.ethiopianorthodox.org

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቀረቡ ከመተሐራ ስኳር ማምረቻ ድርጅት ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤ/ክርስቲያን ዲያቆን ዕፁብ አእምሮ ናቸው ።

1ኛ/ የዲቁና መዓርግ በብዙ ሰዎች ዘንድ በንቀት ዓይን ይታያል ለምን ?

● ዲቁና የሚናቅ ማዓርግ አይደለም ። በመሠረቱ አንድ ሰው ዲያቆን መሆን የሚገባው በቂ የቤተክርስቲያን ትምህርት ሲኖረው ነው እንዲህ ካልሆነ ምና ልባት ይናቅ ይሆናል ።

2ኛ/ በሰበካ ጉባኤ ውስጥ ቃለ ዓዋዲው በሚያዝዘው መሠረት ሳይሆን በግል አስተሳሰብ አባሎች ለምን ይመረጣሉ ?

● የሰበካ ጉባኤ ዓባላት በቃለ ዐዋዲው መሠረት እንጂ ከዚያ ውጭ የሚመረጡ ሁሉ ሕጋዊ አካልነት አይኖራቸውም ከካህናት 6 ከምእመናን 6 ከወጣቶች 2 መመረጥ እንደሚገባቸው ቃለ ዐዋዲው ያዝዛልና ይህ እስካልሆነ ድረስ እርስዎ የጠቀሱት ምርጫ ትክክለኛ ስለማይሆን ትርፉ መካሰስና ጭቅጭቅ ነው ።

እኔ ያለሁበት ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው በከባድ እንዱስትሪ አካባቢ እንደ መሆኑ መጠን ብዙ ወዛደር ይገኝበታል በየቦታው እየተዘዋወሩ ወዛደሩን እንዶ ያስተምሩ የሦስት ሰባክያን በጀት ቤተ ክህነት የፈቀደ ሲሆን ነገር ግን የሠለጠነ ሰው እንዳይላክ በማድረግ የሰው ግን ባር ሲያዩ እንደ ድኩላ የሚበረግጉ መነኩሳትን እያስፈለገ እነሱንም በየወሩ እየቀየረ ምእመናኑን እረኛ የሌለው መንጋ ያደረገ ግለ ሰብ አለ ይህ ሁሉ ሲሆን የቤ ክርስቲያን መሪዎች ለምን ዝም ይላሉ?

● የሠለጠነ ሰባኪ ስለ አለመላኩ ጉዳይ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴን ይመለከታልና ለእኛ ያቀረቡትን ጥያቄ ለእርሳቸውም ቢያቀርቡላቸው መልካም ነው ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ በጌታ በኢየሱስ ስም ሰላምታ አቀርባለሁ ። ቀጥሎም በሕሊናዬ የሚጉላላውን ጥያቄ እጠይቃለሁ ።

1. አንድ ዲያቆን በዜማ በአቋቋምና በቅኔ ቤት በሚቆይበት ወቅት ለአቅመ አዳም ይደርስና በድፍረትም ሆነ በስህተት ከሴት ጋር ይተዋወቃል ከዚያ በኋላ ወደ መኖሪያ ቤቱ ተመልሶ በተክሊል አግብቶ ቄስ ይሆናል ታዲያ ይህ ልክ ነው? ወይስ ካህናት ሁሉ በድንግልና ኖረው ያገባሉ ?

2. ለአንድ መቅደስ ምን ያህል ቄስ? በሚለው ሦስት ሰዎች ይብቁ የሚለውን ሃሳብ በበኩሌ እደግፋለሁ ። ይሁን እንጂ ቃለ እግዚአብሔር ድምቀተ አልባ መሆኑን አንርሳ ።

ተማሪ ገ/ሐና ገበየሁ
ፍቼ ሸዋ

● ተማሪ ገ/ሐና ገበየሁ ስለአንደኛው ጥያቄህ ዲያቆን ከማግባቱ በፊት ከሌላ ሴት ጋር ሩካቤ ከፈጸመ በኋላ እንደገና ሌላዋን ሴት በተክሊል አግብቶ ቄስ መሆን በፍጹም አይችልም ። እንደዚህ ያለውን ቤ/ክርስቲያናችን አትቀበለውም ቀሳውስቶቻችን ሁሉ በድንግልና ያገቡ ናቸው ።

በሁለተኛው ጥያቄህ በአንድ ቤ/ክርስቲያን ሦስት ካህናት ቢሆኑ ቃለ እግዚአብሔር ድምቀት እንደማይኖረው ጠቁመሃል ። ለዚህ መፍትሔው ምእመናኑ ሁሉ የተሰጥዎው ተካፋዮች እንዲሆኑና ያሬዳዊ መዝሙር መዘመር እንዲችሉ በቅድሚያ ማስተማርና ማስተባበር ያስፈልጋል ።

***

ለትንሣኤ ሥጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ የክርስቶስ ሰላምና ፍቅር ከእናንተ ጋር ይሁን እያልኩ የሚከተለውን ጥያቄ አቀርባለሁ ። 1ኛ አንዳንድ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን አድሃሪ ናት እያሉ ሲነቅፉአት እንሰማለን ፤ አድኃሪ ሊያሰኛት የቻለው ምንድን ነው? እንደ ሚባለው ሴቶች በቤተ ክርስቲያን እንዳይናገሩ ስለምታደርግ ነው ?

ተማሪ ስንቅነሽ አስፋው
ከቅዱስ ሚካኤል ወጣቶች መንፈሳዊ
ማኅበር ይርጋ ዓለም ሲዳሞ

● ተማሪ ስንቅነሽ አስፋው ስለ ጥያቄሽ እናመሰግንሻለን ። ቤተ ክርስቲያንን አድኃሪት ናት የሚሉ ልክ አይደሉም ። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ማለት ክርስቲያኖች ወይም ምእመናን ማለት ነው ። ስለዚህ ብዙ ክርስቲያኖች በተራማጅነት አብዮቱን ሲከተሉ ያልነቁትንም ሲያነቁ ይታያሉ። ቤተ ክርስቲያን ከአብዮቱ ጐን ተሰልፋ ትራመዳለች እንጂ አብዮቱን የጐሪጥ አታየውም ። ከኅብረተሰብ ተለይታ መሂጃ በር የላትምና የክርስትና እምነት መጽሐፍትን ብትመለከቺ የሶሻሊዝምን መርሆ ቃላት ይዞ ታገኛለሽና ማን በብ ትችያለሽ ለምሳሌ፡- "ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል ፤ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ------በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም በሀሰት አትክሰሱ ደመወዛችሁ ይብቃችሁ" (ሉቃ 3፡10-14/ "ያመኑት ሁሉ አብረው ነበሩ ያላቸውንም ሁሉ በአንድነት አደረጉ ---------- ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር" (የሐዋ. 2፡44-45) "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" (2ተሰሎ 2 ፡ 10) ታዲያ እንደዚህ የምታስተምር ቤተ ክርስቲያን አድኃሪት ልትባል ይገባል? ሴቶችንም ቢሆን አልተጨቆነችም ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅዱስ አገልግሎት እንዲያገለግሉ መልካም ነገር እንዲያስተምሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይፈቅዳል (ቲቶ 2፡3) ።

ወደ ገጽ ፮ ዞሯል



# ርእሰ አንቀጽ

## እውነት ያሸንፋል

ለማንኛውም ፍጡር ተቃራኒ አለው የዕውቀት ተቃራኒ ድንቁርና ፣ የደግነት ተቃራኒ ክፋት ፣ የብርሃን ተቃራኒ ጨለማ ሲሆን የእውነትም ተቃራኒ ሀሰት ነው ።

ጉዳዩን ለመጠቆም ያህል እንጂ ተቃራኒ ያላቸው ነገሮች ሁሉ በተጠቀሱት ብቻ ይወሰናሉ ማለት አይደለም ፣ ይሁን እንጂ አሁን በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የምፈልገው ስለ እውነት ነው ፣ እውነት ሊደበቅ የማይችል የትክክሎች ተግባራት ሁሉ መመርመሪያ መሣሪያ ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ትምህርት ሲሰጥ በተራራ ላይ የተቆረቆረች ከተማ ከሰው ልትሠወር አትችልም እንዳለ እውነትም ከማንኛውም ሥራ ከፍ ያለ ስለሆነ ለመሠወር አይችልም ።

በዚህ ግዙፍ ዓለም እውነት እየመነመነ ሀሰት እየዳበረና እየወፈረ ከመሄዱ የተነሣ የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑ ሁሉ እውነትን ፈልጎ ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ሆኖ ይታያል ፣ በይበልጥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የእውነት መሪና አስተማሪ በመሆኗ እውነትን ለማያውቁ ወገኖች ለማሳወቅ ከፍ ያለ ጥረት ማድረግ ይገባታል ፤ ወደኋላችን መለስ ብለን የታሪክ ዐምዶችን ስንመለከት የሰው ልጆች ከመዓርጋቸው የወደቁት ከክብራቸው የተዋረዱት እውነትን ጠልተው ወደ ሀሰት በተማጸኑበት ወቅት መሆኑን በጉልህ እንረዳለን ።

ከዚህ ላይ አንድ ጥንታዊ ታሪክን እንመልከት በጥንት ዘመን ዳርዮስ የሚባል የፋርስ መሪ ነበር ፣ ከዕለታት አንድ ቀን ታላቅ ግብዣ አደረገና ብዙ ሰዎችን አብልቶና አጠጥቶ ሲያበቃ ሕዝቡ ወደየቤታቸው ሲሄዱ እርሱም ከሰገነቱ ገብቶ ተኛ ሦስት ባለሟሎች ነበሩት እነርሱም በአንድ ቦታ ተቀምጠው ሲ ጨዋወቱ ከመካከላቸው አንዱ እያንዳንዳችን አንዳንድ ነገር ፈልስፈን ለዳርዮስ እናቅርብና ነገሩ የተወደደለትን ዳርዮስ ይሾመው ይሸልመው እንደራሴም ያድርገው አሉ ። በዚህ ሐሳብ ሁሉም ተስማሙና ለዳርዮስ የሚያቀርቡትን ነገር ይፈልጉ ጀመር ብዙ ጊዜ ካሰቡ በኋላ በአንድነት ሆነው ስለፈለሰፏቸው ነገሮች ይነጋገሩ ጀመር አንደኛው ወይን ያሸንፋል የሚል ሐሳብ አቀረበ ፤ ሌላው ደግሞ መሪ ያሸንፋል ሲል ሦስተኛው እውነት ከሁሉም ያሸንፋል የሚለውን ሐሳብ አቀረበ ። እነዚህን የፈለሰፏቸውን ነገሮች ጽፉና ወስደው ዳርዮስ በሚተኛበት ክፍል ውስጥ በጠረጴዛ ላይ አስቀመጡለት ።

ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ደብዳቤውን አንብቦ በእርሱ አስተዳደር ውስጥ የሚኖሩ አዛውንት ሊቃውንትና ባለሥልጣኖች እንዲሰበሰቡ አደረገ ። የተጻፉትንም ቃላት አስነበበላቸው ቃላቱ ከተነበቡም በኋላ የፈለሰፏቸው ሰዎች በሕዝቡና በዳርዮስ ፊት ማብራሪያ እንዲሰጡ ተጠየቁ ።

በመጀመሪያ ወይንና መሪ ያሸንፋሉ ብለው የጻፉት ካብራሩ በኋላ በመጨረሻ እውነት ያሸንፋል የሚለውን ሐሳብ ያመነጨው እንዲያብራራ ተጠየቀና ሲያብራራ "ወይን በደለኛ ያደርጋል ፣ ንጉሥም በደለኛ ነው ሰው ሁሉ በደለኛ ነው ሥራቸውም ሁሉ በደል ነው ፤ ግን ይህ ሁሉ በእውነት ዘንድ የለም ። እነዚህ ሁሉ በበደላቸው ይሞታሉ እውነት ግን ሁልጊዜ ያሸንፋል ፤ እውነት ሕይወት ነው ፣ ለዘለዓለም ፈጽሞ ጸንቶ ይኖራል ፤ በእርሱ ዘንድ ከእግዚአብሔር መለየት ፤ የሰውን ፊት አይቶ ማድላት የለም ።

ነገር ግን እውነት በሐሰት ፣ በክፉ ነገር ፣ በክፉ ሰውም አያድርም ፤ ሰውም ሁሉ የእውነትን ሥራ ይወዳል ፤ እውነት ያደረበት ሰው በፍርድ ጊዜ ሐሰት አይፈርድም ፤ እርሱም ድል ይነሣል ፣ መንግሥት ፣ ኀናንነት የዓለሙ ሁሉ ሰላም በእውነት ይገኛል ፣ እውነት ገንዘቡ የሆነ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን" ብሎ ዝም አለ፡ከዚያም በኋላ በዚያ ተሰብስበው ገለጻውን በጸጥታ ያዳመጡ ሁሉ" እውነት ደግ ነው፡ከሁሉ ይበልጣል፡ፈጽሞ ድል ይነሣል ብለው ተናገሩ ። ይህን የተናገረው ሰውም በዳርዮስ ዘንድ ከፍተኛ ክብርን አገኘ ይህ ሰው የፈለገው ሁሉ ከፍጻሜ ደረሰለት ፤ 2ኛ ዕዝራ 4. 1-42 ይህ ታሪክ የእውነትን አሸናፊነት ለመረዳት የምንችልበት ነው ፤ ጨው የሌለበት ምግብ ጣዕም ሊኖረው እንደማይችል ከእውነት የተለየም ሥራ መሠረት የለውም እውነት ከሁሉ በላይ ስለሆነና አሸናፊነትም ስላለው ሁላችንም ሀሰትን በመጥላት እውነትን የመከተል ፍላጎት ሊኖረን ይገባል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምልዕተ ጸጋ ማርያም

ፍጥረታት ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተለያየ ጸጋ አላቸው ። ይልቁንም መላእክት በእግዚአብሔር ፊት መቆም የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ ሰዎችን የመርዳትና የማማለድ ጸጋ ተሰጥቶአቸዋል ። ነገር ግን ከቅዱሳን ሰዎችና ከመላእክት ሁሉ ይልቅ ቅድስት ድንግል ማርያም በክብር ትበልጣለች ። ከመላ



ምልዕተ ጸጋ ድንግል ማርያም

እክትና ከሰዎች የበለጠ ጸጋና ባላሟልነት በእግዚአብሔር ፊት አላት ። የድንግል ማርያም ክብር ከእግዚአብሔር በታች ከፍጥረታት በላይ ነው መላእክትና ቅዱሳን የክርስቶስ ወዳጆችና ባለሟሎች ስለሆኑ ብቻ እናከብራቸዋለን ። ድንግል ማርያም ግን በጸጋ ላይ ጸጋ የተሰጣት ማለት ከእናትነት ጋር ባለሟልነት ያላት በመሆንዋ እናከብራታለን ሊቁ ማር ኤፍሬም (400 ዓ.ም) ስለ እግዝእትነ ማርያም ክብር ገናናነት እንደሚከተለው ተናግሮአል ፤ "የድንግል ማርያምን ክብር ተናግሮ መፈጸም የሚችል እንደበት ፤ ሰምቶ የሚረካ ጆሮ ፤ አስተውሎ የሚወስን አእምሮ የለም ። ክብርሽን መናገር የሚችል ፣ አንችንም የሚመስል ማንም የለም" ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ክብርዋ በብዛት ተናግረዋል ።

ከዚህም ሌላ ቅድስት ድንግል ማርያምን የምናከብርባቸው ምክንያቶች እጅግ ብዙዎቻ ናቸው ። ቢሆኑም ጥቂቶችን እንደሚከተለው እንገልጣለን ።

1- ድንግል ማርያም ከሴቶች ሁሉ ተለይታ ቡርክት ናት ፤

ይህም በመልአኩ በገብርኤል ቃል ተመስክሮአል ። ጸጋን የተመላች የተባረከች ፤ ከሴቶች ሁሉ በቅድስናዋ የተለየች እግዚአብሔርም ከእርስዋ ጋር እንደሆነ መልአኩ አረጋግጦአል ። ከዚህም በቀር ቅድስት ኤልሳቤጥ የድንግል ማርያምን ቡርክትነት ፣ ብፅዕትነትና የእግዚአብሔር ወልድ እናትነትዋን ከመልአኩ ቃል ጋር አስተባብራ መስክራለች፡ ራስዋ ድንግል ማርያምም ከመልአኩና ከኤልሳቤጥ ቃል በኋላ "እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል" በማለት ተናግራለች ። (ሉቃ 1:26-56)

2- ድንግል ማርያም በእውነት የአምላክ እናት ናት ፤

እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን በፈቀደ ጊዜ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ሥጋና ነፍስን ከርስዋ ተዋህዶ ተወለደ ።

የመድኃኒታችን የክርስቶስን አምላክነት በዓለም ያለች ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ታምናለች ። በዚሁ አንፃር የድንግል ማርያምን የአምላክ እናትነት አምና ትመሰክራለች ። ምክንያቱም በላይ እንደገለጥነው ከእርስዋ የተወለደው ሀ አምላክ ነው ፤ ሮሜ 9 ፤ 5 ለ እግዚአብሔር ነው የሐዋ 20 ፤ 28 ፤ ሐ ወልደ እግዚአብሔር ነው ገላ 4 ፤ 4

የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም የድንግል ማርያምን የአምላክ እናትነት በግልጥ አስተምረዋል ፤ ለምሳሌ ፦ አግናጥዮስ (200 ዓ.ም.) "አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል ማርያም ማኅፀን ተፀነሰ" ብሎአል ። (ኤፌ.18፣2 አግ) ሌሎችም ኢራንዮስ ሂጶሊጦስ የቂሳርያው ኤሴብዮስ እትናቴዎስና ኤጵፋንዮስ ወዘተ ድንግል ማርያም የአምላክ እናት መሆንዋን አረጋግጠው ከመጻሕፍቶቹውም በላይ ተቃዋሚዎችን አውግዘዋል ።

3- ቅድስት ድንግል ማርያም ከኃጢአት ንጽሕትናት

ማርያም ቅድስት ድንግል ከኃጢአት ሁሉ ንጽሕት እንደሆነች ቤተ ክርስቲያን ታምናለች ። ለዚህም መልአኩ "ምልዕተ ጸጋ ሆይ ደስ ይበልሽ ኤልሳቤጥም "ቡርክት ነሽ" በማለት የተናገሩት ቃል መሠረታዊ ማስረጃ ነው ። ሉቃ 1:28-41 ቅዱስ ያሬድ (500 ዓ.ም) ድንግል ማርያም ኃጢአት እንደሌለባት ሲናገር "ማርያም ግን በአዳም ባሕርይ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራለች" ይላል (ድጓ ዘልደታ) በጠቅላላ የግሪክና የላቲን ሌሎችም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ድንግል ማርያም ያለ ኃጢአት መወለድዋን ያምናሉ ።

4- ድንግል ማርያም ከሐልዮ (ሀሳብ) ከመናገርና ከተግባር ኃጢአት ንጽሕት ናት

መላእክትና ሰዎች ከማሰብ ኃጢአት ቢነጹ ከመናገር ኃጢአት አይነጹም ። ከመናገር ቢነጹም ከተግባር አይነጹም ድንግል ማርያም ግን ከሁሉም ንጽሕት እንደሆነች ቤ ክርስቲያን ታምናለች ።

5. የቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና

ሀ ቅድመ ፀኒስና ወሊድ (ከመፅነስና ከመውለድ በፊት)

ለ ጊዜ ወሊድ (በመውለድ ጊዜ ሐ ድኅረ ወሊድ (ከመውለድ በኋላ ዘለዓለማዊት ድንግል ናት ። ቅ ማርያም ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደወለደች ከለወለደችም በኋላ በድንግልና እንደ ኖረች ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ ። ኢሳ 7:14 ማቴ 1:18:22 ሉቃ 1: 34 ቅዱስ ኤፍሬም "ኮሎ ጊዜ ንጽሕት ሁልጊዜ ንጽህት ነሽ" በማለት ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን ይመሰክራል ። በሐዋርያትና በሦስቱ መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት ሥርዐተ ሃይማ

ወደ ገጽ ፲ ዞሯል



# ክርስቲያናዊ ሕይወት



ደጉ ሳምራዊ በወንበዴዎች እጅ አደጋ ለደረሰበት መንገደኛ ርዳታ ሲያደርግ

በምድር ላይ ለሚኖር ፍጡር ሁሉ የተፈጥሮ ጓደኛ አለው፡ ማንኛውም ፍጥረት ነጠላ ብቸኛ ሆኖ አልተፈጠረምና ይሁን እንጂ የፍጥረታት ሁሉ ጓደኝነት የተለያየ ይዘትና አመለካከት ይኖረዋል።

በተለይም በሰዎች ዘንድ ያለ ጓደኝነት በትምህርት በሀብት፣ በዕድሜ፣ በጾታና በመሳሰሉት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሆኖ ይታያል። ይህም አብዛኛውን ጊዜ አሁን ብረዳው ቆይቶ አጸፋውን ይመልስልኛል፣ ዛሬ ይህን ብሰጠው ነገ ከእርሱ ዘንድ የበለጠ ወይም ተመሳሳይ ርዳታ አገኛለሁ በሚል አስተሳሰብ በጥቅም ላይ የተመሠረተ ጓደኝነት ሆኖ ይገኛል። ታድያ የጥቅሙ ልውውጥ ሁል ጊዜ አይሳካምና በአንደኛው በኩል አነስ ያለ እንደሆነ ጓደኝነቱም ያንሳል ፍቅሩም ይቀዘቅዛል።

በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የፈለግሁት የዓለም ሰዎችን ጓደኝነት ወይም ጠቅላላ የፍጥረታትን ጓደኝነት ሳይሆን በተለይ በክርስትና ሕይወት ጓደኝነት እንዴት ነው? የክርስቲያኖችስ ጓደኝነት በምን ላይ መመሥረት ይገባዋል? በዕድሜና በደረጃ? በሀብትና በጥቅም ልውውጥ ብቻ ወይስ ከዚህ ሁሉ ነፃ የሆነ ርዳታና አገልግሎትን በመስጠት? ይህ ጥያቄ የክርስትናን ሕይወት በመሠረተው በመድኃኔታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶአል።

አንድ ቀን አንድ የሕግ ሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መምህር ሆይ የዘለዓለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ ሲል ጠየቀው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስም በሕግ የተጻፈው ምንድን ነው? እንዴትስ ታነባለህ? አለው ሰውየውም ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ በፍጹም አሳብህም ውደድ፣ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው ኢየሱስም እውነት ተናገርህ ይህን ብታደርግ በሕይወት ትኖራለህ አለው።

ሰውየው ግን ራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ስለፈለገ ባልንጀራዬስ ማን ነው? ሲል ኢየሱስን ጠየቀው ኢየሱስም በምሳሌ ያስረዳዋል ምሳሌውም እንዲህ የሚል ነበር። አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ ፣ በመንገድ ላይ ሳለ ወንበዴዎች አገኙትና ልብሱን ገፍፈው እርሱን ደብድበው በሕይወትና በሞት መካከል ትተውት ሄዱ። ወዲያውኑ በድንገት አንድ ካህን በዚያ መንገድ ሲያልፍ ቁስለኛውን አየው ምንም ርዳታ ሳያደርግለት አልፎ ሄደ ።

እንዲሁም ሌላ ሌዋዊ ቁስለኛው በወደቀበት በኩል ሲያልፍ ቁስለኛውን አየው ግን ምን ይሆናል እርሱም እንደ ካህኑ በቸልታ አልፎት ሄደ እንጂ ምንም አይነት ርዳታ አላደረገለትም ፤ አላዘነለትም ከዚህ በኋላ አንድ ሳምራዊ በዚያ በኩል ሲሄድ ቁስለኛውን አየውና አዘነለት፣ ወደ ቁስለኛውም ቀርቦ ዘይት ቀብቶ ቁስሉን አሠረለት፣ ከዚያ በኋላ በአህያው ላይ አስቀምጦ ወደ እንግዶች ማደርያ ቤት ወስደው በዚያም ሲረዳውና ሲጠብቀው አደረ።

በማግሥቱ ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና አደራህን ጠብቀው፣ ከዚህም በላይ ስለ እርሱ የምታወጣው ወጭ ቢኖር እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው፣ ስለዚህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ቁስለኛ ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል? አለው? ሰውየውም ምሕረት ያደረገለት ነዋ አለ ኢየሱስም ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ በማለት ክርስቲያናዊ ጓደኝነት እንዴት እንደሆነ አስረድቶ

ከዚህ በላይ በተመለከትነው ትምህርት የክርስቲያኖች ጓደኝነት በፍቅር ፣ በመሥዋዕትነት ፣ በሰውነትና ከብድር ነፃ በሆነ ርዳታ መመሥረት አለበት ማለት ነው መቼም ማንኛውም ሰው የብቸኝነትን ኑሮ ማቋቋም ስለማይችል የግድ ጓደኛ ያስፈልገዋል ፣ ነገር ግን ሳይቀበል የማሰጥ ፣ ሲያምኑት የማይክድ ፣ ራሱን ብቻ



www.ethiopianorthodox.org

የማይወድ ጓደኛ ማን ነው ? በክርስትና ሕይወት ውስጥ ጓደኝነት ሳይቀበሉ መስጠት ፣ የታመመውን መጎብኘት የደከመውንና ያዘነውን ማጽናናት በጠቅላላ ርዳታ ለሚፈልጉት ሁሉ በተቻለ መጠን መርዳትና ማገልገል ነው ። ክርስቲያናዊ ጓደኝነት ራስን ከመውደድ ነፃ የሆነ የኅብረተሰብ አገልግሎት ነው ። ክርስቲያናዊ ጓደኝነት በሀብትና በዕውቀት በዕድሜና በደረጃ በዘርና በጾታ ብቻ ሳይወሰን ለደከሙና ለታመሙ ለታረዙና ለተራቡ የሚሰጥ አገልግሎት ነው ። የጓደኝነትን ትርጉም የተረዳ አንድ ሰው "ጓደኝነት አንዱ ሌላውን ለማስደሰትና ለመጥቀም የሚደረግ መልካም የሆነ የሁለት ሰዎች ጊዜ ነው" ብሏል ። ክርስቲያናዊ ጓደኝነት የበሽታውን በሽታ የድሃውን ድኅነት አይጸየፍም በሽተኛውን ያክማል ድሃውን ይጐበኛል ። ክርስቲያናዊ ጓደኝነት ማገልገያ እንጂ መገልገያ አለመሆኑን ክርስቲያኖች ሁሉ ሊገነዘቡት ያስፈልጋል ። የክርስትና ሕይወት አላማውና መሠረቱ አገልግሎትና መሥዋዕትነት ነውና ።

ራድ. አስረስ

---

## ምልዕተ ጸጋ ማርያም

ከገጽ ፬ የዞረ

ኖት "በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም በተወለደው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን" ተብሎ የተጻፈው ውሳኔ የቅድስት ድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና ያረጋግጣል፡

6- የድንግል ማርያም አማላጅነት

የዓለም መድኅን ክርስቶስ ከርስዋ ስለተወለደ ድንግል ማርያም በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የደኅንነታቸው መሠረት ናት ክርስቶስ ዓለምን ያዳነ ከርስዋ በተዋሐደው ሥጋ ነውና ቅ ያሬድ ይላል "አምላክ ከአንች ሰው ስለሆነ ባንች ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ቀረብን" የቤተ ክርስቲያን አባቶች የድንግል ማርያምን የሕይወት መሠረትነት ለመግለጥ ከሔዋን ጋር በማነፃፀር የተናገሩትን ዐረፍተ ነገር ብንጠቅስ ጠቃሚ ይመስለናል "ሔዋን በትእዛዝ ተላላፊነትዋ ለራስዋና ለሰው ዘር ሁሉ የሞት ምክንያት ሆነች ድንግል ማርያም ግን በታዛዥነትዋ ለራስዋና ለሰው ዘር ሁሉ የሕይወት ምክንያት ሆነች ። (ኢራንዮስ) የድንግል ማርያም አማላጅነትዋ በዐፀደ ሥጋና በዐፀደ ነፍስ ላሉት ሁሉ ነው ። ምክንያቱም እግዝእትነ ድንግል ማርያም በኃይለ እግዚአብሔር ከሞት ተነሥታ በሕይወት ስላለች ለሞቱትና በሕይወት ላሉት ሁሉ ከልጅዋ ከክርስቶስ ዘንድ ትማልድላቸዋለች ። ስለዚህም የቀደሙት አባቶች እንደሚከተለው አስተማሩን "ለሰው ልጆች ሁሉ ምሕረትን የምትለምኚ ንጽሕት ድንግል ማርያም ሆይ ወደ ልጅሽ ወደ ክርስቶስ ለምኚልን" (ኤፍሬም) እግዚአብሔር የመረጠሽ ማርያም ሆይ ለምኚልን" (ያሬድ) መድኃኒታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ድንግል ማርያምን በዮሐንስ በኩል የሁላችን እናት እኛንም የርስዋ ልጆች አድርጎ አወራርሶናል እንግዲህ እናታችን እንደ መሆንዋ ትራራልናለች ታማልደናለች ይቅርታንም ታሰጠናለች በዓለም ያሉ እናቶች ሁሉ ልጆቻቸውን ከሚወዱበት ፍቅር እግዝእትነ ማርያም እኛን የምትወድበት ፍቅር ይበልጣልና ።

ማጠቃለያ፡- ስለ እመቤታችን ክብር እንኳንስ በመጽሔት በብዙ ተከታታይ መጻሕፍት ብንጽፍም ለመወሰን አንችልም ። ግን ንጽሕናዋን ጸጋን የተመላች መሆንዋን የአምላክ እናትነትዋን ዘለዓለማዊ ድንግልናዋንና አማላጅነትዋን በአጭሩ በመጥቀስ ስለ ክብርዋ ምስክርነታችንን እንሰጣለን ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፪ የዞረ

ከዚህም ጋር በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ አንድ ናቸውና ቤተ ክርስቲያን በጾታ ምክንያት ልዩነትን መፍጠር አይገባትም

ምንአልባት ባለፉት ጊዜያት ከአገልጋዮችዋ ቸልተኝነትና ከሥርዓቱ መዛባት የተነሣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስ ስወቅስ ሥራ ተሠርቶ ሊሆን ይችላል ።

ስለዚህ የሀገሪቱ ሥርዓት መለወጥ ቤተ ክርስቲያንንም እውነተኛ አገልግሎት እንድትሰጥ ስለረዳት እውነተኛውን አገልግሎትዋን ጀምራለች ፣ ወደፊትም እንደምታስተካክል አንጠራጠርም ።

★★★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

በመጀመሪያ ጸጋና ሰላም ይብዛልህ ፤ ትንሣኤን ማንበብ ከጀመርኩ በርከት ብሏል ስለሆነም ደስታዬ እጥፍ ድርብ ነው ። ከመመልከቴ የተነሣ ጥያቄ ማቅረብ ግድ ሆነብኝ ።

ጥያቄዎቹም እነሆ ፡-

1ኛ/ 29/8/18 አዲስ አበባ የሆነች መኪና እያሽከረከረ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ለገብረ ሰላም በዓል በቅድስት ሥላሴ ቤ/ክርስቲያን ያየሁት በርግጥ ዲያቆን ነወይ? ከሆነ እጅግ ደስ ያሰኛል ምክንያቱም የእኛ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ምንም እንደማይሠሩና እንደማያውቁ ስለሚገመቱ ዲያቆናት በአሁኑ ጊዜ በዚህ ዓይነት ሥራ ሲሠማሩ ደስ ያሰኛል እኔ ያለሁት ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር ስለሆነ በጣም ይንቁናል ቢሆንም ትንሣኤንና ሌሎቹን እያነበብኩ አጸፋውን እመልሳለሁ ። ብዙም አልሰንፍ ።

2ኛ/ በቅርብ የታተመው ትንሣኤ የሲኖዶሱን ሕግ አውጥቷል ለምን በሌላ የራሱ የሆነ (ሲኖዶስ) በሚል ርእስ አታሳትሙም ነበር ። እነዚህን ሁለቱ ጥያቄዎች በተለይ የዲያቆኑን አድራሻውንና የሕይወት ታሪኩን ጭምር በሚቀጥለው እትማችሁ አውጣው በጣም ጠቃሚ ነው ፤ ምክንያቱም ለአለሁበት መሥሪያ ቤት ብዙ ጊዜ የእናንተን መጽሔት በራሴ ገንዘብ እየገዛሁ ስለማስነብባቸው ብታወጣው መልካም ነው ፤ ታይፕ የማደርጋቸው ሁሉ ብታያቸው የእነሱ ዲያቆናትና መነኩሳት በመኪና ሲያርሱ በመኪና ተጉዘው ስብከት ሲሰብኩ የሚል ዜና ሁልጊዜ ስለማነብ ነው ፣ የእኛንም ማስነበብ ስለሚያስፈልግ ይህ

ወደ ገጽ ፯ የዞረል

ችን ደብዳቤ ልልክልህ ቻልኩ ።

ስለሁሉም በሥራችሁ እግዚአብሔር ይርዳችሁ ፤

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ከኢትዮጵያ ጋር ትቅደም የመጽሔቱ ተከታታይ

ወይዘሪት ትበርህ ኮከብ ከደሴ

● ወይዘሪት ትበርህ ኮከብ የመጽሔታችን ተከታታይ ስለመሆንሽ እናመሰግናለን ልብሰ ተክህኖ ለብሶ መኪና ሲያሽከረክር ያየሽውን ዲያቆን አድራሻና የሕይወት ታሪክ ለመግለጽ አልቻልንም ምክንያቱም የመኪናው ታርጋ 29818 አ.አ. የሆነው ባለንብረት ስም ለማግኘት አልቻልንምና ፤

ስለዚህም ዲያቆኑ በተጠቀሰው የመኪናቸው ታርጋ ቁጥር መልእክታችንን ተከታትለው አድራሻቸውንና የሕይወት ታሪካቸውን እንዲሁም ፎቶግራፋቸውን ቢልኩልን በሚቀጥለው መጽሔታችን ለማውጣት ዝግጁ ነን ።

የዲያቆኑ መኪና ማሽከርከር እስከዚህም አስደናቂና እንግዳ ነገር ሊሆን አይችልም ምክንያቱም አብዛኞዎቹ የቤተ ክርስቲያን ልጆች መኪና ከማሽከርከር የበለጠ ብዙ ሥራ ለመሥራት የሚችሉ ናቸውና ነው ። የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ምንም እንደማይሠሩና እንደማያውቁ አድርገው የሚገምቱ ከእሉ ተሳስተዋል ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚያውቁ ልጆቿን አይንቁም ፣ የማያውቅ ግን ቢንቅም ባለማወቁ ነውና አይፈረድበትም መለስ ብሎ ታሪክን ማስታወስ ያስፈልጋል ኢትዮጵያን ከሚያኮሩአትና ከሚያስመኩአት ጥንታውያን ቅርሶችና የታሪክ ዕቃዎች አብዛኞዎቹ በቤተ ክርስቲያን ሰዎች የተሠሩ መሆናቸው አይካድምና ።

2ኛ/ የሲኖዶሱ ሕግ በትንሣኤ መጽሔት እንዲወጣ የተደረገው መጽሔቱ የቤተ ክርስቲያን መጽሔት ስለሆነ በመጽሔቱም ቢወጣ "ሲኖዶስ" በሚል ርእስ ቢታተምም ምንም ልዩነት የማያመጣ መሆኑ ስለታመነበት ነው እንዲሁም ወደፊት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሲኖዶሱ ራሱን ችሎ እንዲወጣ መደረጉ አይቀርምና ተከታታለን እንደምንልክልሽ ተስፋ እናደርጋለን ።

★★★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ በዮሐ. ወ.ም. 10 ከቁ. 11-14 እንዳስረዳው ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሊሆን የሚገባው ራሱን ለበጎቹ አሳልፎ የሚሰጥ እንጂ ቤተ ክርስቲያንን የሚያሳድድና መንጋዎቹን የሚበትን እንዳልሆነ የታወቀ ነው።

ይህንን ለማለት ያበቃኝ በአንዳንድ የቤ ክርስቲያን አሊቃና በካህናቱ መካከል በየዕለቱ የሚደረገውን ኢክርስቲያናዊ ተግባር በመመልከቴ ነው ።

በትንሣኤ ቁ. 18/1971 ዓ. ም. የገዳማት አመሠራረት እንዴት ነው? በሚለው ርእስ እንደተገለጠው አንዳንድ የደብር አለቆች በደጅ ጥናትና በአማላጅ ይሾሙና ክህናት ሳይቀበሏቸው ምእመናንም ሳያምኑባቸው በተፅዕኖ ብቻ የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም የቂም በቀል መወጫ ይሆናቸው ዘንድ አንዳንድ የዕለት ጥቅም ያታለላቸውን የዋሆች መጠቀሚያ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም የሥራ ፍሬ ሳያሳዩ ሥልጣንን መከታ በማድረግ ለጠማማና አስተዋይነት ለራቀው አስተዳደራቸው ተገዥዎች ሆነው የሚፈጸመውን ተንኮልና ዓመፅ ሳያጋልጡ በአርምሞ እንዲቀመጡ ለማድረግ ይመስላል ስንቶቹን ሐቀኛ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችንና ምእመናንን በተኑ ታዲያ የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚሆን ይህን ተግባር መፈጸም ይገባዋል? መልካም ምሳሌነቱስ እምኑ ላይ ነው ?

አንድ አለቃ ካህናቱ በግል ጠልተውት ሳይሆን በተጨባጭ ማስረጃ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ የሆነው ሥራው አጋልጦት እንዲሻር አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ እውነት ተክዳ በአማላጅ ብዛት ብቻ ተቀጭው ቀጭና ክርስቶስ በደሙ የሰበሰባት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን በታኝ መሆን በተለይ ዓለምን ንቂያለሁ ብሎ ለመነኩሰ ተገቢ ነውን ? በአሁንስ ጊዜ እንደዚህ ያሉ መሪዎች ያስፈልጋሉን ? የመንበረ ፓትርያርክ ጽ ቤትስ ምን አስተያየት ይኖረው ይሆን ? መልሳችሁን በጉጉት እጠባበቃለሁ ።

ሃይማኖት ታደሰ

ከአዲስ አበባ

● ሃይማኖት ታደሰ ጥያቄዎ ወቅታዊ ነው ። በአሁኑ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ ያለ ችግር ነው ጥፋቱ የአለቆች ብቻ ነው ለማለት አንችልም በእውነት ከተመለከትን ስህተት በሁለቱም ክፍል ሊኖር ይችላል ። ስህተቶችም የሚፈጠሩት በጠባብ ብሔረኝነት በንቃተ ሕሊና ጉድለትና በሥልጣን ሽሚያ በግል ጥቅም ፍለጋ ነው ቤተ ክርስቲያን ይህን እስካላረመች ድረስ ለችግሩ መፍትሔ አይኖርም በአንድ ዓመት ውስጥ 3እና 4 አለቆችን የለወጡ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ማንም ያውቃል ታዲያ ሦስቱ ወይም አራቱ አለቆች ሁሉ ጥፋተኞች ናቸው ሌሎች ካህናት ግን ትክክለኞች ናቸው ለማለት የሚቻል አይመስለንም ። ስለዚህ ሁሉም ተስተካክለው በደለኞች ስለሆኑ ጥፋታቸውን ሊያርሙና ቤተ ክርስቲያንን ሊመሩ ይገባቸዋል እንላለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፡ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፡ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ

ስልክ ቍጥር 11-66-16

የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ምን እንርዳዎ ዓምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ የመማር ፍላጐትም አለኝ ግን ምንም ረዳት ስለሌለኝ ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገድጃለሁ ።

በዚህ መካከል ደግሞ የተለያዩ ግለሰቦች ለሚስትነት እየጠየቁኝ ነው ።

ከእነዚህም ውስጥ 1ኛ ገንዘብ ያለው ፡ መኪና በየቀኑ የሚቀያይር ነጋዴ ለጋብቻ ጠይቆኛል ። 2ኛ ደግሞ ዲግሪ ያለውና ከፍተኛ ደሞዝ ያለው በመልኩም አስደሳች የሆነ ወጣት ጠይቆኛል ። ሌላው ሶስተኛው ደግሞ መጠነኛ ደሞዝ ያለውና በኑሮውም ይህን ያህል ተደሳች ያልሆነ ጠባዩ ግን በጣም የተመሰገነና እንከን የሌለው ነው እነዚህ ሁሉ ለጋብቻ ጠይቀውኛል ።

በዚህ ምክንያትም ማንኛውን መከተል እንዳለብኝ በጣም የተቸገርኩ ስለሆነ ምን እንርዳዎ በሚለው ዓምድ መፍትሔውን ትገልጹልኝ ዘንድ በጉጉት እጠባበቃለሁ ።
ወ.ት አዛለች ዓለሜ

ወይዘሪት አዛለች ዓለሜ የአንቺ ችግር የብዙዎች ችግር ነው ። የዘመኑም ወጣት የሚለው ይኸው ነው ።

ስለሆነም ዛሬ ብዙ ሴት ላጤዎች የብቸኝነትን ኑሮ መርጠው ሳይወልዱ እናት ሆነው የሚታዩት ከጠያቂው ብዛት ሲያማርጡ ጊዜው እያለፈባቸው ነው ።

ከዚህም ሌላ ከማማረጥ ብዛት ሌላ ነገር ስለሚለምዱ ትዳር ይህና ዋይ ያሉት ጥቂቶች አይደሉም ።

ከብዙ ወንዶች ጋር ከመዋል የተነሳ እስር ዓይነት ጠባይ ሲያማርጡ ሳያገቡ ከእንግዲህ ባል በቃኝ የሚሉትም ቁጥራቸው እየበረከተ ሄዶአል ።

እንዲህ ዓይነቶቹ ሴቶች ‘‘መራጭ ይወድቃል ከምራጭ’’ እንደሚባለው በመጨረሻ ጊዜ የሚወድቁበት አስደሳች አይሆንም ።

ብቻ እንዲህ ዓይነቶቹ ሴቶች ምርጫቸው ካገኙት ጋር መዞር ስለሚሆን በመጨረሻ በዙረት የሚያገኙትን ቢያገቡም እንኳ ኑሮአቸው ጭቅጭቅ ፡ ጥርጥርና ቅንአት የሞላበት ስለሚሆን የተገናኙበትን ቀን ሲረግሙ ዕድሜአቸውን ይጨርሳሉ ።

ስለዚህ አንቺም እንዲህ ዓይነቱ ዕድል እንዳይገጥምሽ አስቀድመሽ በነገሩ ስለአሰብሽበት የምትመሰገኚ ከመሆንሽም በላይ ትዳርሽም የተቃና ሊሆን ይችላል ።

የትምህርትሽ ደረጃ 10ኛ ክፍል ድረስ መሆኑን ገልጸሻል ። ብቻ የሚረዳኝ የለም አልሽ እንጂ ትምህርትሽን እስከመጨረሻ ድረስ ብትከታተይ ከሁሉም በላይ የተሻለ ነበረ ።

ቢሆንም ለመማር የምትችይበት ዘዴ ካለ ሞክሪ ፡ ካልቻልሽ ግን ለትዳር ከመደብሻቸው መካከል በገንዘቡ ብዛት በትምህርቱም ከፍተኛነት ሳይሆን የትዳር መሠረቱ መልካም ጠባይ ስለ ሆነ በጠባይ ብልጫ ያለውን ሰው በሚገባ ተከታትለሽ እጥኚ የመኪናው መቀያየር ፡ የገንዘቡ ብዛት የመልኩ ማማር ፡ ትዳር ሊሆን አይችልም። ጠባይ ከሌለ ትርፉ የሚያሳድጉበት ገንዘብ ሳይኖር ልጅ አንጠልጥሎ መውጣት ነው።

መልካም ጠባይ ካለው ግን ‘‘ጕመን በጤና’’ ነውና ባለው ተደስታችሁ ሀብት ማፍራት ትችላላችሁ ።

በእርግጥ ሀብት ያለው ሁሉ ጠባዩ መጥፎ ነው ማለት አይደለም ፡ ምንም ሀብት የሌለውም ሙልጭ ያለ የጠባይ ድሀ ሊሆን ይችላል ነጋዴ መሆንም ነውር አይደለም ። አሁንም ታላቁ ነውር ጠባይ ማጣት ነው።

አንዳንድ ወንዶች ደግሞ እጅ እስከሚያደርጉና ከጋብቻ ውጭ የፈለጉትን እስነዋሪ ፍትወተ ሥጋ እስከሚፈጽሙ ድረስ የታዘዙትን ሁሉ እሺ እንትትን ግዛልኝ ፡ ውይ! ለንቺ! ኧረ ምኑ! በጠቅላላ የሚለወጥ ጠባይ የያዙ አይመስሉም ። ታዲያ የፈለጉትን ከፈጸሙ በኋላ ስልክ ቢደወል የሉም ፡ ቢሮ ቢኬድ፡ አልገቡም በጠቅላላው ይደበቃሉ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ወንዶች በየቦታው የልጆች አባት ናቸው ለማሳደግ ግን ወይ ፍንክች ከእንዲህ ዓይነቶቹ ምላሳ ለስላሶች የትዳር ነቀርሳዎች የታዳጊ ሴቶች መቅሰፍቶች መጠንቀቁ ብልህነት ነው።

ስለዚህ አንችም ለትዳር የምትመርጫቸው ሰዎች ምን ዓይነት መሆናቸውን በጥንቃቄ ማጥናት አዋቂነት ነው ።

መኪናው አይማርክሽ፡ ጠባይ ከሌለው የአንች አይደለምና የገንዘቡ ብዛት አያስጐምጅሽ ብታይው እንጂ አይሰጥሽም። በጠቅላላው የምትመርጭው ሰው የሚመጣጠንሽ ፡ ልብሽን ካገኘበኋላ የማይንቅሽ፡ የሚያስተምርሽ የእኩልነት መብትሽን የሚረዳ መሆን አለበት።

አንችም አስቀድመሽ ለመረጥሽው ሰው ሌላ የፍቅር ግዳጅ ለመፈጸም አትሞክሪ፡ ውደጅው እንጂ በሌላ በኩል የሚጠይቅሽን ለመፈጸም አትሞክሪ። ምንም ብትወጂው ከጋብቻ በፊት ሕገ ጋብቻ አትፈጽሙ በተረፈ መልካም ትዳር ከእግዚአብሔር ነውና እግዚአብሔር መልካም ትዳር እንዲሰጥሽ ዘወትር በጸሎት ጠይቂው እኛም መልካም ትዳር እንዲሰጥሽ እንመኛለን።



# ይህን ያውቁ ኖረዋል ?

ከእጅጉ ረታ

ለመሆኑ ጾም ለመጀመሪያ ጊዜ በየትኛው ሃገር ? መቼና ? እንዴትስ ? እንደተጀመረ ያውቃሉን ? ለአንዳንድ አንባቢዎች ጥያቄው ቀላል ሊመስላቸው ይችላል ፡ ግን ቀላል አይደለም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የክርስትና እምነት ተከታዮች ሊቃውንት በዓለም ላይ የታወቁትን ሃይማኖቶች በማገናዘብ ፡ ሠፊ ጥናት አርገው እስካሁን ገና ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት አልቻሉም ።

ጾም መቼና እንዴት ተጀመረ ከሚለው ጥያቄ ይልቅ ሰጾሙ መጀመር ምክንያት የሆኑት ነገሮች ከሞላ ጐደል መልስ የተገኘላቸው ይመስላል ። በጠቅላላ አስተሳሰብ ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምሮ በየሀገሩ የሚኖሩ ሕዝብ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሣ ይብዛም ይነስ ተመሳሳይነት ያለው ጾም ይጾሙ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል ። በጥንቱ የአሕዛብ ዓለም ጾም ከአምልኮ ሥርአቶች ጋር የተያዘ ነበር ። ከእነዚህ የአምልኮ ሥርዓቶች አንዱ የበዓል አከባበር ነው ። ለምሳሌ ጥንታውያን የግብጽ ጣዖታት አገልጋዮች በየበዓላቱ መሥዋዕት ከማቅረባቸው በፊት በዋዜማው ዕለት ከእህል ከውኃ ተከልክለው በጾም የማክበር ልማድ ነበራቸው ። ሌላው ሥርዓት ደግሞ በቤተ ጣዖት ውስጥ ይነገር የነበረው ትንቢት ነው ። በተለይ በግሪክ ሐገር በደልፊ የአጵሎን ቤተ ጣዖት አገልጋይ የሆነች ሴት (በሀገራችን አባባል የዛር ፈረስ እንደምንለው ያለ ነው) ትንቢት ከመናገሯ ሦስት ቀን በፊት ጀምሮ ምንም ምን ሳትቀምስ እንደምትጾም በታሪክ ተጽፏል ። በዚያኑ ዘመን በማኅበራዊ ኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ለሚደርስ ደስታም ሆነ ኃዘን ጾም ድርሻ ነበረው ።

የጥንቱ ዘመን ጋብቻ ከመፈጸሙ አንድ ቀን አስቀድሞ ተጋቢዎቹ ይጾሙ እንደ ነበርም ታውቋል ። ዘመድ በሞት በሚለይበት ሰዓት ለቀስተኛው መሪር ኀዘኑን የሚገልጠው ለረዥም ጊዜ እህል ውሃ ሳይቀምስ በመጾም መሆኑም ተረጋግጧል ። የዚህ ዓይነቱ ልማድ ቅሬታ ዛሬም በሃገራችን በአንዳንድ ቦታዎች በትልይም በገጠር ከቤተሰብ ፡ ከቤተ ዘመድ ፡ ከጐረቤት ወይም የቅርብ ወዳጅ ሲሞት ግብዓተ መሬቱ እስኪፈጸም ድረስ እህል ውሃ አይቀመስም እርም ነው ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጥያቄውን በሌላ መልኩ ላቅርበውና ጾምን የሚያወግዝ ሃይማኖት መኖሩን ያውቃሉን ? ከሆነ መልካም ፡ የማያውቁ ቢሆን ግን ይኸውልዎ ዞሮአስትሪዝም ይባላል ። መሥራቹ ዞሮ አስትር ወይም ዛራቱስትራ በፋርስ (ኢራን) ሰባት መቶ ዓመተ ዓለም ከክርስቶስ ልደት በፊት ተነሳ ። እሱም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የጣዖት አምልኮ ነቅፎ ፡ ዓለማትን የፈጠረ አንድ አምላክ መኖሩን አስተማረ ።

በዞሮአስትሪዝም እምነት መሠረት፡

ሀ የብርሃን መላእክትና የጨለማ አበጋዞች (ሰይጣናት) ፡

ለ የነፍስ ዘለዓለማዊነት (ኢመዋቲነት) ፡

ሐ የሙታን ትንሣኤ ፡

መ ጽድቅና ኩነኔ መኖራቸው ይታመናል ። በዚህ አንጻር ሲመለከቱት ትምህርቱ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል ።

ከፍ ብለን እንዳየነው ከሆነ ግን የእጆቻቸው ሥራዎች የሆኑትን ጣዖታት የሚያመልኩ አሕዛብ ፡ የጾምን ጠቃሚነት ተረድተው ሲፈጽሙት ዛራቱስትራ ግን ጾምን አጥብቆ ተቃውሟል ። ተከታዮቹም እንዳይጾሙ ከልክሏል ።

በሌላ አንጻር ሲታይ ደግሞ የጾሙ ወቅት ፡ የአጿጿሙ ዓይነትና ሥርዓት ይለያይ እንጂ ፡ በዓለም ላይ ብዙ ተከታዮች ያሏቸው ታላላቅ ሃይማኖቶች ሁሉ ጾም አንድ ሰማያዊ በረከትን የሚያስጥ የተቀደሰ ተግባር መሆኑን አምነው ተቀብለዋል ።

በጠቅላላው የሕንዱ ሃይማኖት ብራሕማዊ ሲሆን ፡ በውስጡ ልዩ ልዩ ክፍሎች አሉት ፡ ዋና ዋናዎቹ ግን ጇይዝምና ቡድሂዝም ናቸው ። በእነዚህ ሃይማኖት የተደነገገው የጾሙ ሕግ እጅግ ጥብቅ ነው ። በክረምቱ ወቅት ለአራት ወራት የሚጾሙት ጾም አላቸው ። በዚህም ጊዜ ውስጥ ለገዳማውያኑ (መነኰሳት) ቢቻል በሦስት በአራት ቀን አንዴ ፡ ባይቻል ግን በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ተመግበው እንዲጾሙ ሕግ ተሠርቶላቸዋል ። በየወሩም ጨረቃ የምትታይበትን 11ኛውን ዕለትና ሙሉ ጨረቃ የምትሆንበትን 11ኛውን ዕለት ቆጥረው ይጾሙታል ። ሌሎች ሌሎችም አጽዋማት አሏቸው ።

ምንም እንኳ ለእኛ ለክርስቲያኖች የጾሙ ዓይነትና ሥርዓት ልዩ መስሎ ቢታየን በማንኛውም ሃይማኖት ጾም የተከበረ ሕግ ነው ።

ጾም ፍላጐትን ለመግዛት መንፈስንም ሰብስቦ በተቀደሰ ተግባር ላይ ለማዋል ፍቱን መድኃኒትነቱን ሃይማኖቶች ሁሉ ተቀብለውታል ። ጾም ሌላም ጥቅሞች እንዳሉት ታውቋል ።

በክርስትና እምነት ውስጥ ያለው ስፍራስ እንዴት ነው ? ለምንስ እንጾማለን ? በሚቀጥለው ጊዜ የሚቀርበው ጽሑፍ ይህን የሚመለከት ይሆናል ።

ማሳሰቢያ፡- ይህን ጽሑፍ ሳዘጋጅ የተመለከትኳቸው መጻሕፍት ፡

1. ኢንሳይክሎፔድያ ብሪታኒካ ፡
2. ኢንሳይክሎፔድያ አሜሪካና ፡
3. የቤተ ክርስቲያን ኢንሳይክሎፔድያ ፤
4. ማሕአትማ ጋንዲ በራሱ የተጻፈ የሕይወት ታሪክ (አውቶባዮግራፊ) ።




www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ

## ደቅ ናርጋ ሥላሴ

ባለፈው ጊዜ ስለ ጣና ቂርቆስና ዳጋ እስጢፋኖስ በገለጽኩበት ወቅት ናርጋ ሥላሴ ያግል ስም የቤተ ክርስቲያን ስም ጠቅሼ ነበር። ናርጋ ሥላሴ ናቸው። ደቅ አርሴማ በጣም ጥንታዊነት ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት። አርሴማ የተባለች ቅድስት እንደነ ክርስቶስ ሠምራ የመ



በጣና ሐይቅ ውስጥ የሚገኘው የናርጋ ሥላሴ ደሴት

ሰለች በስምዋ ታቦት የተቀረፀላት ቅድስት ሴት ናት። በደቅ አካባቢ የሚኖሩ አረጋውያን ታሪክ አዋቂዎች እንደ ሚሉት ከሆነ በደቅ አርሴማ ውስጥ ብዙ ቅርሳ ቅርሶች ነበሩ ይላሉ ነገር ግን እነዚህ ቅርሶች ቀስ በቀስ ተመዝብረው አልቀዋል እኔም እንደተመለከትኩት በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈውን ወንጌል መጀመሪያ ላይ ሐረግና ሥዕል ያለበትን ሳነብ ከእሉት ቅርሳ ቅርሶች እንደማይነፃር ተረድቸአለሁ ። ከላይ እንደገለፅኩት የደቅ ደሴት ሁለተኛው ቤተ ክርስቲያን ናርጋ ሥላሴ ይባላል። ናርጋ ሥላሴ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመን መንግሥት የተመሠረተ በጣም ዝነኛ የሆነ ቤተ ክርስቲያን ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በራሳቸው በአጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ሲሆን መሪው በዘመናቸው ከሠሩአቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል ዋነኛው በመናገሻ ከተማቸው በጐንደር ከተማ የሚገኘው ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ናርጋ ሥላሴ ነው።

እነዚህም ሁለት አብያተ ክርስቲያናት የሚመሳሰሉባቸው ብዙ ሁኔታዎች አሏቸው። የጐንደር ደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የአሠራር ቅርፅ አራት መዓዘን ቢሆንም ናርጋ ሥላሴ ግን ሦስት ዙሪያ ያለው ክብ የሆነ ሰቀላ ቤተ ክርስቲያን ነው በሌላ በኩል ደግሞ የሚመሳሰሉበት በውስጣቸው በሚገኙ ሥዕሎችና፣ በየእቃ ቤታቸው ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍትና መስቀሎች ብዙ አሉ።


አጼ ኢያሰ አድያም ሰገድ የናርጋ ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን በሰው ክንድ በተፈጠ ድንጋ

ጋ ሥላሴ በጣና ደሴት ደቅ ከተባለው ደሴት ውስጥ ይገኛል። ደቅ የተባለው ደሴት በጣና ባሕር ውስጥ በሚገኙት ደሴቶች የመጨረሻው ትልቅ ደሴት ነው።

የደሴቱ የተፈጥሮ አቀማመጥ የአካባቢው ቅርፅ ያለው ለጥ ያለ ሜዳ ሲሆን የመሬቱ ጠቅላላ ስፋት 20.000 ስኩየር ሜትር ያህል ይሆናል ። የጣና ባሕርና አካባቢው ጠቅላላው የተፈጥሮ አቀማመጥ ቆላማና ወይና ደጋ መሬት ሲሆን ደቅ የተባለው ደሴትም ከባህሩ ውሃ ጥቂት ሜትሮች ብቻ ከፍ ብሎ ቢገኝም ቆላማና ሙቀት የበዛበት ሥፍራ በመሆኑ እንደሌላው ቆላማ መሬት ሁሉ አንዳንድ በሽታ በየአመቱ ይቀስቀስበታል።

ይህ ደሴት ሰፊና ለእርሻ የሚሆን ለም አፈር ያለበት መሬት ነው። በደሴቱ ውስጥ ከብት እያረቡ፣ እርሻ እያረሱ የሚኖሩ ቁጥራቸው ወደ ሦስት መቶ የሚጠጉ ገበሬዎች ይገኙበታል።


እነዚህ ኅብረተሰቦች በጠቅላላው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን የሚከተሉ ክርስቲያኖች ስለሆኑ ክርስትና ሲነሡ የሚጠመቁባቸው ሲሞቱ የሚቀበሩባቸው ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አሉዋቸው እነርሱም ደቅ አርሴማና



የናርጋ ሥላሴ ቤ/ክርስቲያን



ይ እንደ ዘመናዊ ሲሚንቶ በመጠቀም እጅግ ጠንካራ በሆነ አሠራር ቤተ ክርስቲያኑን መሥርተውታል በአገራችን ውስጥ የሲሚንቶ ጥቅም 1ኛ የቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ አካባቢ በተፈጥሮ እፀዋት የተሸፈነና ከአመት እስከ አመት ፍጹም የሆነ ልምላሜ ስለሚታይበት ነው። በ



በቅርፁ አስደናቂ የሆነ ከብርና ከወርቅ የተሠራ የናርጋ ሥላሴ መስቀል

ዚያውም ላይ ልዩ ሁብረ ቀለማትና መልክ ያላቸው የባሕር አእዋፍ በብዛት ስለሚገኙበት በወፎቹ ድምፅና ጫጫታ ከማዕበሉ የመናወጥ ድምፅ ጋር ተደምሮ በክብር የተቀነባበረ መዝሙር ይመስላል።

2ኛ የናርጋ ሥላሴ በሰው ሰራሽ ስሚንቶ በተገነባ ሰፋትና ጥንካሬ ያለው ቤተ ክርስቲያን ከመሆኑም በላይ በቤተ መቅደሱ ጠቅላላ ዙሪያ የተሳሉት የጻድቃን የሰማዕታት የመላእክት ፣ የቅድስት ድንግል ማርያምና የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ታሪካዊ ሥዕሎችን ልዩ ልዩ ኅብር ባላቸው ቀለማት የተሳሉ ሲሆን በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያም የመሪዎች ልዩ መታጠቢያ ቤትና እልፍ እልፍም በእንቁላል ግንብ የተገነቡ የጸሎት ቤቶች ሲታዩ በጣም ያስደስታሉ።


በየክፍለ ዘመኑ በኢትዮጵያ የተነሱ ጠቢባቶች አንዳንድ አስደናቂ የሆኑ ሥራዎችን ያሳዩ ነበር ነገር ግን ለማንም ሰው ሳይተላለፍ ከሰዎቹ እድሜ ጋር አብሮ ተበባቸውም ያልፍ ነበር። በዚህ ረገድ አባቶቻችን ተበበኞች እንደነበሩ ያስገነዝበናል የጠበብትነታቸው ምልክት እልፍ እልፍ የሚታዩት አስደናቂ ሥራዎቻቸው በግልጽ በጠቀስነው ቦታ ይገኛሉ።

ስለዚህ በናርጋ ሥላሴ ውስጥ በጣም የሚደነቁ ታሪካዊ ቅርሶች አሉ እነሱም ሀዊ የተባለው መጽሐፍና ከወርቅና ከብር የተሰራው የእጅ መስቀል ናቸው መጽሐፈ ሀዊ ሦስት እምድ ያለውና የብራናው ጥራት ንጣት ባይን የሚያንፀባርቅ የብርዕ አጣጣልና የፊደሉ አቀማመጥ በጣም የሚያስደንቅ ነው መስቀሉ ደግሞ ከብ

ምና ሙያ ጉላ ብሎ የታወቀው ከፋሺሽት ኢጣልያ ወረራ ወዲህ ነው። ነገር ግን ቀደም ባሉ ዘመናት እጅግ ባይበዛም በሰው ጉልበት የተፈጨ ሲሚንቶ በአገራችን ይሠራበት እንደነበረ በአጼ ኢያሱ የተሠራው ናርጋ ሥላሴንና በእቴጌ ምንትዋብ የተሠራውን በጐንደር ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን አስተውሎ መመልከቱ ይበቃል።

የናርጋ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክረምት ወራት ደሴት ሆኖ ይከርማል ይህም ማለት የቤተ ክርስቲያኑ አቀማመጥ ከዋናው የደቅ ደሴት ትንሽ ወደባሕሩ ሾጠጥ ብሎ የገባ መሬት ስለሆነ ባሕሩ በክረምት ወራት እየሞላ ስለሚሄድ ከዋናው ቤተ ክርስቲያን በስተቀር ዙሪያው በውሃ ተከቦ ይከርማል። ካህናቱም በክረምት ወራት ወደቤተ ክርስቲያኑ ሲገቡ በጣር ታንኳ እየቀዘፉ ይገባሉ።

ናርጋ ሥላሴ የአገር ውስጥ ጐብኝዎችም ሆኑ የውጭ አገር ጐብኝዎችን መንፈስ የሚማርክበት ብዙ ነገሮች አጠቃልሎ ይዞአል ። ይኸው



በናርጋ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የሚገኝ 400 ዓመት ዕድሜ ያለው ግንብ



www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፡ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፥፫) ።

ጠባይዐ እግዚአብሔር
7 የትክክለኛ ፍትሕና ርትዕ ባለቤት ስለመሆኑ

እግዚአብሔር አምላክ ቅዱስ ፍጹም ጻድቅና ንዑሐ ባሕርይ ስለሆነ በማንም ላይ በሐበተና በአድልዎ አይፈርድም ። ዕውነተኛ በመሆኑ ለሁሉም በትክክል ይፈርዳል ማለት ነው ።

ስለዚህም ሕግ ተላላፊውን ሁሉ እንደ ሥራው ይፈርድበታል ። ለሕግ ፈጻሚውም በዕውነት ያለሐሰት በሥራው መጠን ይፈርድለታል ። ደኃውን አይንቅም ፣ ባለጸጋውንም በሀብቱ ብዛት አያከብረውም፣ ሁሉንም የሚፈርድበት ወይም የሚፈርድለት በሥራው መጠን ብቻ ነው ።

ከዚህም የተነሣ ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲናገር "በዕውነት አስተዋልሁ እግዚአብሔር የሰው ፊት አይቶ አያዳላም አለ ። (የሐዋ ሥ. 10፥35) ክርስቶስም ራሱ ስለአብ ሲመሰክር "ጻድቅ አባት ሆይ !" ብሎ እንደጠራው በዮሐ 17፥25 እናያለን ። ቅዱስ ጳውሎስም በበኩሉ "እንግዲህ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል እርሱንም በዚያች ቀን የሚሰጠኝ ያ ዕውነተኛ (ጻድቅ) ፈራጅ እግዚአብሔር ነው ሲል ጽፎአል ። (2 ጢሞ 4፥8)

የእግዚአብሔር ዕውነተኛ ፍርድ በዚህ ዓለም እንኳ ይታወቃል ። ማለትም እርሱን ያመኑ በርሱ ስም የተማጸኑ መልካም ዋጋቸውን ሲያገኙ አመጸኞች ግን መከራ ሲደርስባቸው ይታያል ።

ስለዚህም ነበር የይሁዳ መሪ የነበረው ኢዮሣፍጥ "በየአንዳንዱ ከተማ ፈራጆችዳኞችን ከሾመ በኋላ "እንግዲህ ተመልከቱ እግዚአብሔርን የመፍራት ጥበብ ይኑራችሁ በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አድልዎና በደል የለም ። መማለጃ ጉቦ መቀበልም የለምና ሁሉን ነገር ተጠንቀቃችሁ አድርጉ" ሲል የተናገረ (2 ዜና 19፥6-7)

8ኛ ስለ ፍጹም ፍቅሩ

ልዑል እግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር ነው፤ ይህም ፍጹም ፍቅሩ በፍጥረት ሁሉ ላይ ሠፍኖ እንዲኖር ፈቃዱ ነው ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ የሰውን ዘር ለማዳን ወደዚህ ዓለም መምጣቱ ራሱ የፍቅሩን ጽናት አጉልቶ ያሳያል ። ስለዚህም ነበር አንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ "እግዚአብሔር ይህን ዓለም ከፈጠረበት ጥበብ ይልቅ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ዓለምን (የሰውን ዘር) ያዳነበት ጥበብ ይበልጣል" ሲል የመሰከረ ።

አዎ ወንጌላዊው ዮሐንስ (3/6) እንደ ጻፈ "እግዚአብሔር እንዲሁ ዓለምን ወዶታልና አንድ ልጁን ቤዛ (ለውጥ) አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ ሁሉን ነገር ፈጽሞአል ፤ ይኸውም የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ በርሱ የሆነ ሁሉ እንዳይጠፉ በመወሰኑ ነው ። አባ ሕርያቆስም "ኃያል የሆነ ወልደ እግዚአብሔርን ስቦ ለመስቀል ሞት ያበቃው ፍጹም የሆነ የሰው ፍቅር ወይም ለሰው ልጆች ያለው ፍጹም ፍቅር ነው ብሏል ።

በሌላም በኩል ሥጋዬን ብሉ ፣ ደሜን ጠጡ ብሎ የሰጠው የቃል ኪዳን ማኅተም የፍቅሩ ምልክት ስፋት መግለጫ ነው ። በዓለም ላይ ይህን ያደረገ ማንም ስለሌለ ለፍጹም ፍቅሩ ተነፃፃሪና ተወዳዳሪ የለውም ከዚህም ከፍቅሩ ጽናት የተነሳ ኃጢአተኞችን ለመቅጣት አይቸኩልም ፈጥኖም አይቀስፍም ንስሐ የሚገባበትንና ወደ ጽድቅ መንገድ የሚመለስበትን ወራት አብዝቶ ይሰጠዋል እንጂ ሮሜ 2፥7-5 ።

ቄስ መክብብ አጥናው

---

ርና ከወርቅ መሠራት ብቻ ሳይሆን በመስቀሉ ሁለት ገጽ ላይ የመላእክት የጻድቃን ፣ የማርያም ሥዕሎች ቅርፅ የተቀረፀበት አስደናቂ መስቀል ነው።

ከላይ እንደገለፅኩት ሁሉ የናርጋ ሥላሴ በተፈጥሮ ውበትና ሰው ሰራሽ ድምቀት በቱሪስት ድርጅት በግልፅ በመታወቁ ኢትዮጵያን ለመጐብኘት የሚመጡት የውጭ አገር ቱሪስቶች እንደጎበኙትና እንደተረዱት እንደ አንድ መደበኛ የታሪክ ሥፍራ ሆኖ ናርጋ ሥላሴ በመመደቡ በቤተክርስቲያን ጥግ የጀልባ ማረፊያ ተበጅቶለት በየአመቱ በመቶ የሚቆጠሩ ቱሪስቶች በአድናቆት ይጐበኙታል።

ግርማ ኤልያስ

## ማሳሰቢያ

በየአብያተ ክርስቲያናቱ የደረሰውን የልብሰ ተክህኖ ችግር ለማቃለልና ለማስወገድ በሥራ ጥናትና ዕቅድ መመሪያ ተጠንቶ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተፈቀደ፣

1ኛ/ በመናገሻ አውራጃበዓለም ገና ወረዳ አስተዳደር ፣ በሰባታ ቤተ ደናግል ጠበባት ገዳም ።

2ኛ/ በመንበረ ፓትሪያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት ግቢ የልብሰ ተክህኖ ማደራጃና ማከፋፈያ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ተቋቁሞ ሥራው በጥሩ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ነው ።

የተቋቋመበትም አላማ ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ የሚሆኑትን ንዋያተ ቅዱሳት የቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ ጽ/ቤት እያዘጋጀ በልብሰ ተክህኖ በኩል ያለውን ችግር ለማቃለልና ምእመናንንም በከፍተኛ ዋጋ ከነጋዴዎች ከመግዛት ለማዳን ነው።

ስለዚህ የአምስት ልውካን ልብሰ ተክህኖ ዋጋ ብር 200 መሆኑን እየገለጽን ፈላጊዎች በጠቅላይ ቤተ ክህነት እየመጡ መግዛት የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን ።

«ኢትዮጵያ ትቅደም»

ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል
የዕቅድና ጥናት ኃላፊ
ስልክ 12-49-09
ፖ.ሣ. ቁ. 12-83



# የኢትዮጵያ ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች

ካለፈው የቀጠለ ክፍል 3
የሡልጣን ሲሌም ፈርማ የቱርክ ንጉሥ ነው

በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስትያን መታደስ አባ ዮሐንስ ሐናስ/ በተባሉ ኢትዮጵያዊ አሳሳቢነት



የኢትዮጵያ ምእመናን በዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም

በ1ሽህ400 ዓ.ም ተጀመረ። የማሳደሻውም ወጭ ከኢትዮጵያ መንግሥት ከሕዝበ ክርስትያኑም ነው የኢትዮጵያውያን ርስታቸውና ቤተ ክርስቲያናቸው ገዳማቸውና በየቦታውም ያላቸው ክፍል ብዙ ነው። ከዚህም በጎልጎታ ውስጥና በውጭውም ያለ ቦታቸውን ለይቶ የሚያስረዳ የነገሥታትና የአገር ገዥዎች ፈርማ በሐበሾች እጅ ይገኛል። የኢትየጵያውያን ሕዝብ በተለይም የእነሱ የሚሆን(የሆነ) የሚጸልዩበትም ሁሉ በኢየሩሳሌም በእነሱ ስም የታወቀ እንደሚከተለው ነው።

ይሄውም 7 ቀን ዲል የሚያበሩበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተገነዘበት ላይ ደግሞ 7 ቀን ከሚያከብሩበት የጌታችን ትንሣኤ ዕለተ ብርሃን ከሚወጣበት ውስጥ የኢትዮጵያውያን ቀንዲል መስቀያ አንዱ ወደ ደቡብ ሲል ሁለተኛው ደግሞ ወደ ሰሜን ያለው ነው። ደግሞ በዚሁ በጎልጎታ ውስጥ በምሕዋሩ መመላለሻ የሚገኙ 3ት ክፍል ቤቶች በተለይ የሐበሾች የሆኑት በደቡብ በኩል ናቸው። ከዚሁም ላይ ያለች ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ስም የታወቀች ናት በሷም ላይ የሚገኙት የመብራት ፋኑሶች በሰሜን በኩልም በምሕዋሩ ያሉ 2ት ክፍል ቤቶች ደግሞ በደኅናው ጥርብ ዕንጨት የተሠራ ቤትና በዚሁም የሚገኘው መቅደስ ጌታችን ከተነሣበትና ከምሥራቅ መካከል ሆኖ በዚሁ በተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን የሚገኝ ነው በዚሁም የሚገኙት የቀንዲል ፋኑሶች የዚሁም በር መዝጊያው ጥሩ በሆነ ጥርብ ዕንጨት ነው። ይህ የተቆጠረ ሁሉ በተለይ የእነርሱ ነው። በዚሁም በኢየሩሳሌም ከሚገኙት ክርስቲያኖች ሁሉ ከኢትዮጵያውያን በስተቀር የሚገባበት የለም በሀገሩ ሕግ በተወሰነው መሠረት የጸና ነው።

### የጎልጎታ ይዞታ

በጎልጎታ የተያያዘ በስተደቡብ በኩል በምድር ቤት የሚገኘው የሐበሻ ቤተ ክርስቲያን ነው ። በሩም ወደ ደቡብ የሆነና ትልቁ ገዳም ዴር ሡልጣንም የዚሁም ገዳም መግቢያ በር በጎልጎታ ደጃፍ አደባባይ ነው ። በዚሁም ገዳም ዙሪያ የሚገኘው ቦታ ሁሉ መኖሪያውና ቤቶቹም ሁሉ የካህናት አልባሳት ማኖሪያ በተቆለፈው ትልቁ ሰንዱቅ ውስጥ ያለ ነው። ይህም ደግሞ በዚሁ በተጠቀሰው ገዳም የሚገኘው ከከፍተኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ። ይህ ሁሉ በዝርዝር የተጻፈ የሐበሻ ይዞታ ነው። ከዴር ሡልጣን ከተያዘችው የእሌኒ ቤተ ክርስቲያንም የኢትዮጵያውያን ናት። ሡልጣን ሳሊም ይህ ከላይ የተጻፈው ለንጉሡ ቀርቦ የተነገረ በዚሁ በተወሰነው ትእዛዝ መሠረት ይህ የተቀደሰው ትእዛዝ የጸና ይሁን ። ይህን ትእዛዝ አፈርሳለሁ ብሎ ለመቃወም የሚሞክር ከልዑል እግዚአብሔር ሰይፍ በታች ይውደቅ ። በተወዳጁ ነቢይና በእግዚአብሔር ረዳትነት ወደ ተቀደሰችው የፈጣሪያችን ከተማ (ለማየት) መጣሁ ። ሰፈር በሚባለውም ወር በ25 ቀን 1923 ዓመተ ሕጅራ በ15




በዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም
የአርባዕቱ እንስሳ ቤ/ክርስቲያናችን



www.ethiopianorthodox.org

17 ዓ.ም አዋጁን ነግሬ ፈጽሜ ነገሥ ኩባት አለ። ይህም ቃል የሕግ መሪው አገረ ገዥ ከንጉሡ የተነገረውን አዋ



በኢትዮጵያውያን ቁጥጥር ሥር የሆነው የቅ/ሚካኤል ቤ/መቅደስ በዴር ሡልጣን

ጅና ከላይ የተጠቀሰውን ትእዛዝ በጥን ቃቄ ተቀብሎ እንደ ደንቡ አስመዘገበው።

ከዚህም በኋላ ከኢትዮጵያውያን መነኰሳት የተሾመው ወኪል ለማናቸውም ምክንያት ትእዛዙ በእጁ ሁኖ ማስረጃ እንዲሆነው የዚህ አዋጅ ግልባጭ ይሰጠኝ ሲል ጥያቄ አቀረበ። ጥያቄውም በመስከረም ወር 1550 ተፈቀደለትና ትክክለኛው ግልባጭ ተጽፎ ተሰጠው።

ለዚሁም አስረጅ የምስክሮቹ ስምና ፊርማ ሡልጣን ሰሊማን (ኮፒው ከፎቶግራፍ የተነሣ ነው)

1ኛ ከኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ወገን አባ ገብረ ክርስቶስ ሐበሻ

2ኛ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ወገን ሊቀ ጳጳሳት ጀርማኖስ ግሪክ

3ኛ ከአርመን ሕዝብ ወገን ሊቀ ጳጳሳት ስር ቤስ አርመን

4ኛ ሸክ መስቶፋ ዘካርያስ የጦር ሠራዊት ኃላፊ

5ኛ አል ሸክ ኑር ዲንና የኢየሩሳሌም አገር ገዥ ኹሴን ፓሻ

6ኛ የተከበሩ የኢየሩሳሌም ቃዲ አሕመድ ሐሰቢ እብን አል ባሕኒና ሸክ መሐመድ እብን ሸኽ አብደል ቃድር አል ሸሐቢ እብን አል ሸኽ ሙሔድ ዲን አል ኑአማን። አልሸፋኢ ሸኽ አል እስላም ቀድሞ ሙፍትሕ የነበሩ ለቅዱሱ ቦታ መሥሪያ ቤቶች

7ኛ ዘራፍ ሙስቱፋ ፓሻ ናቸው በዋናው በተሠራበት ቋንቋ መሠረት በቱርክ ቋንቋ ተረጋግጧል። ፊርማ የኢየሩሳሌም አገረ ገዥ ምክትል።

በዚህ ማስረጃ መሠረታዊ ቦታችንን ያገኘንበት ነው። ሆኖም በ1942 ዓ.ም በዶክተር ካልዲ ሑሴን የቅዱሳት ቦታዎችና የሃይማኖት ዳኛ አባ ያዕቆብ የግብጽ ጳጳስ በኢየሩሳሌም በማስረጃው አርዕስት በስመ እግዚአብሔር ሕያው ቅዱስ እግዚአብሔር አሐዱ አምላክ የሚለውን ቃል የእስላሞች አይደለምና ማስረጃው መንግሥት ሊቀበለው አይገባም ብሎ በማቅረብ ክፍ ያለ ክርክር አድርገናል። ይሄውም ተከታትለን የበለጠና እውነተኛ ማስረጃ በ1400 ዘመን ኢየሩሳሌምን ይገዙ የነበሩ ነገሥታት ዓረቦች ሳይሆኑ መማሊክ የተባሉ መሆናቸውን ታሪክ ፈለስጤን (የፍልስጥኤም ታሪክ ክብረ ነገሥታት) አቅርበን ከገጽ 216 እስከ 232 የተመዘገበው እውነተኛነታችንን አረጋግጠልናል። የሡልጣን ሰሊምም ከገጽ 232 ክፍል 72 በ1517 ዓ.ም በተጠቀሱት አል መማሊክ የተባሉ ነገሥታት የተመዘገበው ቀርቦለት በፊርማው ያጸደቀው ነው። እንዲሁም ሡልጣን ሰሊም ኡመር እብን አልኸጣብ በሰጠው ውሳኔ መሠረት እንዲጸና በግሪክ መሪነት የኩርጅና የሐበሻ በክብር እንዲጠበቅ አዟል ይህም የሰጠውን ትእዛዝ ታሪክ ከኒሳት ኡሩሻሌም (የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን) ታሪክ ከተባለው ከገጽ 110 እስከ 111 የተመዘገበውን ከማረጋገጡም በላይ የመንግሥት የርስት ክፍል መዝገብ ቁጥር 151 ገጽ 7 በደንብ ተመዝግቦ ስለተገኘ በጆርዳን መንግሥት ተወስኖልናል።



የኢትዮጵያውያን ቀደምትነትን በሚያስረዳው በግእዝ ቋንቋ አቡነ ዘበሰማያት ተጽፎ ከሌሎች ጥንታውያን ቋንቋዎች ጋር በደብረ ዘይት ይታያል



# ለቤተ ክርስቲያን ማሳተሚያ ድርጅቶች በምሥራቅ ጀርመን ሴሚናር ተደረገ

ባለፈው ሚያዝያ ወር 12-21 71 ዓ.ም. በኅብረተ ሰብአውያት ሀገሮች ላሉ የቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ አሳታሚዎች ኅብረተ ሰብአዊት በሆነችው በዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ ጀርመን ውስጥ ኸርን ሁት በተባለ ቦታ ሰሚናር ተደርጐ ነበር። በሰሚናሩ ላይ ከ




30 በላይ የሆኑ በማሳተም ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች ተገኝተዋል። ከኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያም

1. አቶ ዘመድሁን ብዙ ወርቅ የሐዋርያዊ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ

2. አቶ እሱባለው ወ/ሥላሴ የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤትና የማሳተሚያ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ

3. አቶ አማረ ማሞ የምሥራች ድምፅ የሥነ ጽሑፍ ድሬክተር የነበሩ

4. አቶ ተስፋዬ ዳባ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በሰሚናሩ ላይ ተገኝተው ተካፍለዋል። የትንሣኤ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም በላይ ለጠቀስናቸው የሥነ ጽሑፍ አሳታሚ ድርጅት ኀላፊዎች ስለ ሰሚናሩ እንዲሁም ስለክርስቲያናዊ የሥራ ሂደት በዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ጀርመን ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸዋል።

ጥያቄ፦ ወደ ምሥራቅ ጀርመን የሄዳችሁበት ዓላማ ምን ነበር?

መልስ፦ በሶሺያሊስት ሀገሮች ላሉት የቤተ ክርስቲያን ነክ ሥነ ጽሑፍ አሳታሚዎች በተደረገው ሰሚናር ላይ ለመገኘት ነበር።

ጥ. የሰሚናሩ ዓላማ ምን ነበር?

መ. የሰሚናሩ ዓላማ በሶሺያሊስት ሀገሮች ያሉት የክርስቲያን ጽሑፍ አሳታሚዎች የሚያሳትሙአቸውን የሕትመት ዓይነቶች ለመመርመርና ሥራቸውን በይበልጥ





በሰሚናሩ ላይ ተካፋዮች የነበሩ አራት ኢትዮጵያውያንና ሌሎችም ሊቃውንቶቻችን



www.ethiopianorthodox.org

ለማሻሻል እንዲችሉ ትምህርት ለመስጠት ነው ።

ጥ. በስሚናሩ ላይ የተካፈሉ ሰዎች ከስንት አህጉር የመጡ ነበሩ?

መ. በስሚናሩ ላይ ተካፋዮች የነበሩ ከምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች ከሩሲያ ከሀንጋሪ ከቼኮዝላቫኪያ ፣ ከምሥራቅ ጀርመን ፣ ከፖላንድ ፣ ከቡልጋሪያና እንዲሁም ከአፍሪካ ከኢትዮጵያና ከማዳጋስካር የሄዱ ናቸው ።

ጥ. ቤተ ክርስቲያን በኅብረተ ሰብአዊት ጀርመን የክርስትና እምነትን ለመስበክና ወንጌልን ለማስፋ



ስሚናሩ የተካሄደበት ሕንጻ በኀርን ሁት

ፋት ምን አይነት ዕድል አላት?

መ. በመሠረቱ ፦ በኅብረተ ሰብአዊት ጀርመን ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ህልውና በሕገ መንግሥት የታወቀ ከመሆኑም በላይ ሙሉ ነፃነት ከመብት ጋር ተሰጥቷታል። ከዚህም የተነሣ፦ ልዩ ልዩ መጽሔቶችን ጋዜጦችንና መጻሕፍት በማሳተም የክርስትና እምነትን ታስፋፋለች ።

ጥ. ከኅብረተ ሰቡ ጋር ለመገናኘትና ለወጣቱ ትውልድ ክርስትናን ለማስተማር ሌላ ምን አይነት ዘዴ አላት?

መ. ኢኮኖሚንና ሶሺያልን በሚመለከት ጉዳይ እንደዚሁም ስለ ኅብረተ ሰቡ ኑሮ እድገት ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ተሳትፎ አላት ። ለምሳሌ ከሰባት ሽህ በላይ አልጋዎች ያሉዋቸው 50 ሆስፒታሎች ሠርታ በሃይማኖት ምክንያት ልዩነትን ሳትፈጥር ለማንኛውም ታካሚ አገልግሎትዋን ታበረክታለች ። ይህ ብቻ ሳይሆን የአእምሮ መታወክና የአካል ጉድለት በሽታ ላለባቸው ሰዎች 90 መኖሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ከ6000 አልጋዎች ጋር ለተጡዋሪ ሽማግሌዎች 330 መኖሪያ ቤቶች 11.500 ሰዎችን ከሚይዝ ክፍል ጋር ሠርታ ታገለግላለች ። በእነዚህም ድርጅቶች ውስጥ 15.000 ሰዎችን ቀጥራ ታሠራለች በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን በምሥራቅ ጀርመን ኅብረተ ሰቡን ለማገልገል ታላቅ ተሳትፎ እንዳላት ተረድተናል

ጥ. የኅብረተሰብአዊት ጀርመን ክርስቲያኖች ስለ ሶሺያሊዝም ፍልስፍና ምን አይነት አስተያየት አላቸው?

መ. የኅብረተ ሰብአዊት ጀርመን ክርስቲያኖች የሶሻሊዝም ተቃዋሚዎች አይደሉም ፣ ዓላማቸውንም የዘነጉ አይደሉም ። ከዚህም የተነሣ በ1971 (እ.ኤ) በኤይናክ የተደረገው የመጀመሪያው ሲኖዶስ ሦስተኛ ጉባኤ የሚከተለውን መመሪያ አውጥቶአል ። "ቤተ ክርስቲያን የሶሺያሊዝም ተቃራኒት እንድትሆን አንፈልግም ። ግን በሶሺያሊዝም ውስጥ እንድትሆን እንፈልጋለን "በዚህ መሠረት ክርስቲያኖች ሶሺያሊዝምን የኀሪጥ አይመለከቱትም ወደኋላም ለመቅረት አይፈልጉም ። ሶሺያሊዝም ከእምነት በስተቀር በማንኛውም የፍልስፍናው ይዘት ከክርስትና የሚለይበት መንገድ ስለሌለ ክርስቲያኖችን አያስደነብራቸውም ። ሁለቱም ክፍሎች የሚለያዩበትን የፍልስፍና አይነት ጠብቀው በሚገናኙበት መንገድ በአንድነት ለሀገራቸው ዕድገት ብልጥግናና መሻሻል ይሠራሉ ።

ጥ. በአሁኑ ጊዜ የኅብረተሰብአዊት ጀርመን የሕዝብ ቁጥር 18 ሚሊዮን እንደሚሆን ታውቆአል ። ከዚህ መካከል የክርስቲያኖች ቁጥር ምን ያህል ይሆናል?

መ. ከሀገሪቱ ሕዝብ ግማሹ (9. ሚሊዮን) ክርስቲያን መሆኑ ተረጋግጦአል ።

ጥ. የሰሚናሩ ውጤት ምን ነበር?

መ. ይህ አይነት ሴሚናር ለቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍት አሳታሚዎች በሶሺያሊስት ሀገር ሲደረግ የመጀመሪያ ጊዜ ነው ። የሴሚናሩ ተካፋዮች በየሀገሮቻቸው ስላለው የሕትመት ሥራ እንቅስቃሴ በማስረዳታቸውና አዳዲስ የማሳተም ሥራ ዘዴ በመቅሰማቸው በሴሚናሩ ተደስተዋል ። በመሆኑም ተመሳሳይ ሴሚናር በሌላ የሶሻሊስት ሀገር እንዲደረግ የሴሚናሩ ተካፋዮች ወስነው ጊዜውንና ቦታውን የሴሚናሩ አስተናጋጅ ሀገር ምሥራቅ ጀርመን ከዎርልድ አሶስየሽን ፎር ክርስቲያን ኮሚኒኬሽን (የዓለም ክርስቲያኖች የመገናኛ ዘዴዎች ማኅበር) ጋር ተነጋግሮ እንዲወስን ተብሎአል ። በማለት አራቱ የአሳታሚ ድርጅት ኀላፊዎች አቶ አማረ ማሞ አቶ ተስፋዬ ዳባ አቶ ዘመድሁን ብዙወርቅና አቶ እሱ ባለው ወሥላሴ ገልጠውልናል ።

ሶሺያሊዝም፦ ለሰዎች እኩልነት መብት ፍትሕና ነፃነት የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን ከክርስትና እምነት የሚርቅበት

ወደ ገጽ ፲፯ ይዞሯል



# የጤና ዓምድ

## የቂጥኝ በሽታ

ከአባለ ዘርዕ በሽታዎች መካከል ቂጥኝ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያስከትል በሽታ ነው በደንብ ካልታከሙት የልብ ሕመምን ፣ መታወርን ፣ የአእምሮ ህመምንና ሽባነትን እንዲሁም ሞትን የሚያስከትል ጠንቀኛ በሽታ ነው ፣ የቂጥኝ ህመም ልዩ ልዩ ደረጃዎች አሉት "እነርሱም አንደኛ ደረጃ ፣ ሁለተኛ ደረጃና ሦስተኛ ደረጃ ይባላሉ በየደረጃው ያለው የበሽታው ዓይነትና ምልክቱ እንደሚከተለው ይሆናል።

**የመጀመሪያ ደረጃ ቂጥኝ** ከግንኙነት በኋላ ሶስት ሳምንት ቆይቶ ትንሽ ቁስል በብልት ላይ ይወጣል ፣ ቁስሉ ትንሽ ቡግር መስሎ ሊወጣ ይችላል፣ቁስሉ ሲነካ አያምም ፣ በብልት አካባቢ ንፍፊት ያወጣል ፣ በዚህ ደረጃ ላይም እንዳለ በቀላሉ ሊተላለፍ ይችላል ፡ በሴቶች ላይ በሚወጣበት ጊዜ በማህፀን አካባቢ ስለሚወጣ ቶሎ አይታወቅም ፣ በሽታው ስለ ማይታወቅም ለብዙ ወንዶች በቀላሉ ልታስተላልፍ ትችላለች ሕክምና ባይደረግለትም ቁስሉ ለጊዜው የጠፋ እየመሰለ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ቂጥኝ ይደርሳል በመጀመሪያ ደረጃ ላይ እንዳሉ ለባለቤቱ ካለመታወቁም ሌላ በወንዱም ሆነ በሴቷ ላይ በሕክምና ሲመረመር እንኳ ደም ንፁሕ ሆኖ ሊገኝ ይችላል በሽታው ግን መስፋፋቱን ይቀጥላል በዚህ ዓይነት እየተሰወረ ያለው በሽታ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ሳይደርስ ደግሞ ከአንደኛው ደረጃ የተለየ ምልክት ያሳያል ።

### ሁለተኛ ደረጃ ቂጥኝ፦

በአንደኛ ደረጃ ላይ እንዳለ በሽታው አይታወቅም በደም ምርመራም ጊዜ አይገኝም በዚህ ዓይነት ደረጃ እየተጓዘ በሚደርስበት ሁለተኛ ደረጃ ላይ በግልፅ ይታያል ማለት ነው አፍንና ጉሮሮን ያቆስላል ፣ ቆዳ ላይ ግልብጥ ብሎ ይወጣል ፣ ብልት ላይ ይቆስላል ንፍፊት ያወጣል ፣ የአጥንት መጋጠሚያዎችን ያሳብጣል በዚህኛው ደረጃ መካከል እንዳለ ወደ ስውር ቂጥኝነት ይለወጣል በስውሩ ዓይነት ቂጥኝ ጊዜ በሽተኛው ምንም ህመም አያስማውም ውስጥ ውስጡን ግን ብዙ ጉዳት ያደርስበታል ። ጀርሞቹ በሰውነቱ ተሰራጭተዋል ማለት ነው ወደ ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍሎችም በመዛመት ያጠቃሉ ይህም ለብዙ ዓመት ሊቀጥል ይችላል በስውሩ ቂጥኝ ጊዜ ጀርሞቹ በበሽተኛው ደም ውስጥ ስለሚገኙ የደም ምርመራው በስውር ቂጥኝ መያዙን ያረጋግጣል ። በሁለተኛ ደረጃና በስውር ቂጥኝ መካከል እያለ በቂ ሕክምና ካልተደረገለት ወደ ሶስተኛው ደረጃ ይለወጣል ።

**ሶስተኛው ደረጃ፦** እዚህኛው ደረጃ ሲደርስ የሚያሳየው ምልክትና የሚያደርሰው ጉዳት እንደሚከተለው ይሆናል ።

- ልብንና ትልቁን የደም ቧንቧ በመጉዳት የልብ ድካምንና በመጨረሻም ሞትን ያስከትላል
- የአከርካሪትን ዋና ሥር (ስፓይናል ኰርድ) በማጥቃት ሽባነትን ያመጣል
- አንጐልን በማቃወስ የአእምሮ መታወክን ያስከትላል ።
- የዓይን መታወርን ፣ የጆሮ መደንቆርን ፣ የአጥንት ቂጥኝ ቁርጥማትንና ሌሎችንም በማስከተል ውርዴ ተብሎ ይጠራል እነዚህ ከላይ በአንደኛ፣ በሁለተኛና በሦስተኛ ደረጃ የተጠቀሱት በሽታዎች በዚህ ሁኔታ ላይ ቢደርሱም የሚድኑ ወይም የማይድኑ በሽታዎች እንደሆኑ ለማወቅ ከሕዝብ ጤና ጥበቃ አባለዘርዕ በሽታዎች መታከሚያ ድርጅት አቶ ማሞ ገላጋይን አነጋግረናቸው ነበር ።

ጥያቄ. አቶ ማሞ የቂጥኝ በሽታ የሚድን ነውን?

መ. አዎ በቶሎ ከተደረሰበትና ሕክምና ከተደረገለት በፍጥነት ይድናል ስለዚህ ከላይ ከተዘረዘሩትለሞት ወይም ለመሰናክል ከሚያበቁት የቂጥኝ በሽታዎች ለመዳን ወደ ሐኪም ቤት መሄድ ያስፈልጋል አቶ ማሞን እንደገና በዚህ ከሚታከሙት ሰዎች ውስጥ አብዛዎቹ የተያዙት በቂጥኝ ፣ በሽታ ነው ወይስ በጨብጥ ላልናቸው ሲመልሱ በጨብጥ የተያዙት ሰዎች እንደሚበዙ ነግረውናል።

ከዚሁም ጋር አያይዘን በዚህ ከሚታከሙት ብዛት ያላቸው ሴቶች ናቸው ወንዶች ላልናቸው ሲመልሱ ሴቶች ይበዛሉ ሲሉ መልሰውልናል ለምን? ሴቶች እንደሚበዙ ለጠየቅናቸውም በሽታው በሴቶች ላይ ቶሎ ስለማይታወቅና ለሌሎችም ሳይታወቃቸው ያስተላልፋሉ ሲሉ ከመለሱልን በኋላ በመጨረሻም በየትኛው ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን እንደሚያጠቃቸው ለጠየቅናቸው ሲመልሱ ፣ በሴቶችም ሆነ በወንዶች ላይ ሃያ አምስት ዓመት አካባቢ ያሉት በበሽታው እንደተያዙና በድርጅቱም የሚታከሙት አብዛኞቹ በእዚሁ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉት መሆናቸውን ገልጸውልናል ።

### ማጠቃለያ

የአባለ ዘርዕ በሽታን የሚያመጡት ረቂቅ ተዋሕስያን የተለያዩ ናቸው

የቂጥኝ ጀርሞች ለዓይን የማይታዩ ረቂቅ ናቸው ለማየት የሚቻለው ማይክሮስኰፕ (አጉሊ መነጽር) በሚባለው ብቻ ነው እጅግ ረቂቅ በመሆናቸው በትንሽ የቆዳ ስንጣቂ ወይም በብልትና በአፍ ካለአንዳች ችግር ሊገቡ ይችላሉ የቂጥኝ ጀርሞች ከአካል ውጪ በቀላሉ ይሞታሉ በአካል ውስጥ ከገቡ ግን ለመኖር ኃይል ይኖራቸዋል በተከታታዩ ጽሑፍ ስለአባለ ዘርዕ በሽታዎች በበቂ ሁኔታ ተመልክተናል በተጨማሪ ለመረዳት ጥያቄ ቢኖራችሁ ለጤና ዓምድ አዘጋጅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋርያዊ ድርጅት አ.አ. የመ.ሣ.ቍ. 3137 ብትጽፉልን ይደርሰናል ።

ወ/ት ንብረት አበበ



www.ethiopianorthodox.org

## ሊቃውንቶቻችን

የጋስጫው አባ ጊዮርጊስ

ሊቅ በሚያሰኘው በትምህርት ደረጃቸው በምርምር ስልታቸው በሥነ ጽሑፍ አቀራረባቸው ፣ እንዲሁም በብቃትና በመንፈስ ቅዱሳዊ ሀብት በተቃኘው ሰብአዊ ሁኔታቸው የታወቁ የኢትዮጵያዊው የአባ ጊዮር



ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

ጊስ ዘጋስጫን ታሪክ ከብዙው በጥቂቱ እነሆ በዚህ ዓምድ ላይ እናቀርባለን ።

### ሐረገ ትውልድና ዘመነ ልደት

የትውልድ አገራቸው ትግራይ የሆነው የአባ ጊዮርጊስ አባታቸው ሕዝበ ጽዮን ፣ እናታቸው የወለታ ቦረና ተወላጅ እምነ ጽዮን ይባላሉ ።

ባልና ሚስት የነበሩት ሕዝበ ጽዮንና እምነጽዮን ለረጅም ዘመን በመካንነት ከኖሩ በኋላ የመውለድን ፀረከት እንዲያገኙ እንደ ነቢዩ ሳሙኤል እናት እንደነቢይት ሐና ወደፈጣሪያቸው ኡመለከቱ አባ ጊዮርጊስ በ1357 ዓ.ም. በጥቅምት 3 ቀን ተፀንሰው በዚሁ ዓመተ ምሕረት በሐምሌ 7 ቀን መወለዳቸውን ታሪካቸው ይረጋገጣል ።

### የትምህርት ይዞታቸው

የታሪካቸውን ሒደት በማስመልከት ከታሪክ ተከታታዮች እንደተጻፈው ወላጅ አባታቸው አባ ጊዮርጊስን አባ ሠረቀ ብርሃን የተባሉ የሐይቅ መምህር እንዲያስተምሩላቸው በአደራ ሰጥተዋቸው ሰባት ዓመት ተምረዋል ። ከዚህም በቀር የያሬዳዊ ዜማ ጥናታቸው ሙሉ በሙሉ ተቃንቶላቸው ሊቅ የሚያሰኘውን ከፍተኛ ስም ለመውረስ ችለዋል ተብሎ ይተረካል ዝርዝር ሁኔታው በታሪክ መጻሕፍት ተመዝግቧል ።

### የሥነ ጽሑፍ ችሎታቸው

በሥነ ጽሑፍ ዝንባሌና አቋሙ በዓለም የታወቀው ደራሲው ሰርቫንትስ ‘‘ብዕር የአእምሮ ምላስ ነው’’ በማለት ለድርሰትና ለሥነ ጽሑፍ ተግባር ከፍተኛ ግምገማ እንደሰጠው ሁሉ በብሉያትና በሐዲሳት በመሳሰሉትም ቅዱሳት መጻሕፍት የምሥጢር ባህር ይዋኙ የነበሩት አባ ጊዮርጊስ ሥነ ጽሑፍ የአእምሮ ምላስ መሆኑን በመመዘን በተለያዩ የውጭ አገር ጽሑፎች እንደተገለጸው ሁሉ አርባ የሚሆኑ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ደርሰዋል ።

እነዚህም እስከ ዓርባ ቁጥር የሚደርሱት መጻሕፍቶቻቸው ለከፍተኛ ሊቅነታቸውና ቁም ነገርን ላዘለው ተግባራዊ ውጤታቸው ማረጋገጫዎች ፣ የሥራ ሰው ለመሆናቸውም ታላቅ ማስረጃዎች ከመሆናቸውም በላይ ዕውቀታቸውን በጽሑፍ ያልገለጹትንና የሞያ ቅርሳቸውን በሥነ ጽሑፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያላስተላለፉትን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ወቃሾችና ከሣሾች ናቸው ።

እንግዲህ ይህ እንዳይሆን የዛሬዎቹም ሆኑ የወደፊቶቹ ሊቃውንት ለተከታዩ ትውልድ ስለሚተላለፈው የሥነ ጽሑፍ ቅርስ ሊነቁበትና ሊጠነቀቁበት ይገባል የሚል መልእክት በዚህ አጋጣሚ ተላልፎላቸዋል ።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ከደረሷቸውም መጻሕፍት መካከል 1. አርጋኖን 2. ኆኅተ ብርሃን 3. ውዳሴ መስቀል 4. በ12ቱ ሰዓተ መዓልትና በ12ቱ ሰዓተ ሌሊት በዜማና በንባብ የሚደርስ መጽሐፈ ብርሃን (ሰዓታት) 5 የቤተ ክርስቲያን ፣ የሥላሴ የእመቤታችን የመላእክት የጻድቃን የሰማዕታት የነቢያትና የሐዋርያት ሰላምታ 6. ጸሎተ ፈትቶ 7. መጽሐፈ ምሥጢር ይገኙባቸዋል ።

ከነዚህም ጋር የቅዱስ ያሬድን ዜማ ለራሳቸው አጠናቅቀው ተምረው ለሌላው የሚያስተምሩ እንደመሆናቸው ለዜማው አገባብና አደራረስ ልዩ ልዩ ዓቅድና ሥነ ሥርዓት በመስጠት እጅግ አድርገው የደከሙና ሞያቸውን በሥራ የገለጹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ባለውለታ ናቸው ‘‘ሰው ይሞታል ታሪክ ግን አይሞትም’’ የተባለውም ባህላዊ አነጋገር በቀጥታ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን ይመለከታል ለማለት ያስችላል ።

#### የደረሷቸው መጻሕፍት ከያዙት ፍሬ ነገር በጥቂቱ

አርጋኖን መሰንቆ ወይም ዕንዚራ ማለት ነው ና በአጠቃላይ የልዩ ልዩ ምስጋና መግለጫ ስልት ነው ፣ እንዲሁም ኖኅተ ብርሃን የተባለው እመቤታችን የብርሃን ደጃፍ ወይም የብርሃን መውጫ መሆንዋን በማስመልከት የተሰጠ ስያሜ ነው በመሆኑ ሁለቱም መጻሕፍት እመቤታችን እምላክን ለ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞርአል



## ዜና ሀገረ ስብከት

በአሁኑ ወቅት የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና ለማጠናከር መንፈሳውያን ወጣቶች በሚመለከታቸው ሲጣጣሩ ፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት ምእመናንን በሰበካ ጉባኤ በማደራጀት የድርሻቸውን ሲደክሙና ካህናትም የሚፈለግባቸውን መንፈሳዊ ግዴታ ለማሟላት በኅብረት ሲሠሩ መታየታቸው ለሥራው መቃናት ምስክር ነው።

በዚሁ መሠረት በየቦታው የተከናወኑ አንዳንድ መንፈሳዊ ሥራዎችን እንመለከታለን። በሸዋና ሲዳሞ አህጉረ ስብከት የሚገኙ መንፈሳውያን ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ፍቅር ተመሥርተው ከግንቦት 11 ቀን ጀምሮ በሻሸመኔ ከተማ በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ለሁለት ቀናት የፈጀ ውይይት በማድረግ የተለያዩ ውሳኔዎችን አስተላልፈዋል።

ካሳለፉት ውሳኔዎች የወንጌልን ትምህርት ለማስፋፋት ፣ በሃይማኖት ስም እየተጠጉ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ስም ለማስጠላት ስለሚሯሯጡ ግለሰቦች መፍትሔ መፈለግ ፣ ሰበካ ጉባኤ በይበልጥ እንዲጠናከር ተባብሮ መሥራትና በአጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሚሆኑ ሥራዎችን ለመሥራት በውሳኔ ተስማምተዋል።

በሌላም በኩል በሻሸመኔ የካህናት ማኅበር በየደብሩ በመቋቋም ላይ የሚገኝና የተቋቋመውም የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና በማጠናከር ላይ እንደሚገኝ ከማኅበረ ሐዋርያት አምደ ሃይማኖት ጽ/ቤት መ/ምገስ አባተ ገልጸዋል ።

በጊዜውም መንፈሳዊ ቲያትር በማሳየት 131.00 ብር ገቢ ያስገኙ መሆናቸውን ጨምረው አስረድተዋል ።

በአሁኑ ወቅት በየአብያተ ክርስቲያናቱ በመዘዋወር መንፈሳውያን ወጣቶች ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ቢቀርቡ ለቤተ ክርስቲያን ምን ያህል አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ግልጽ ነው ።

### ሐረር

ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ጳጳስ ዘእጋዴን በሐረርጌ ተገኝተው ሥራቸውን ከጀመሩ በኋላ የጉዴን ልማትና የግብረ ኃይሉን ሠራዊት ጐበኙ ።

ብፁዕነታቸው በጉዴ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ የአውራጃው አስተዳዳሪ ፣ የግብረ ኃይሉ አዛዥ ኮሎኔል ውብሸትና የግብረ ኃይሉ ሠራዊት ተቀብለዋቸዋል ።

‘‘እያመረትን እንዋጋለን እየተዋጋንም እናመርታለን’’ በሚለው መርሆ መሠረት በልማቱ ላይ የተሠማራውን ሠራዊት በጐበኙበት ወቅት ሠራተኛውን በይበልጥ ለማነቃቃትና የሥራን ክቡርነት ለመግለጽ ብፁዕነታቸው ሠርተው በማሳየታቸው ሠራዊቱን አስደስተውታል ።

ብፁዕነታቸው በጉዴ ልማት ገና የሚታረሰውን ፣ ተዘርቶ ፍሬው ወደስዎች አፍ ሊደርስ የተቃረበውን ፣ በጠላት ፈራርሶ የነበረው የግቤ ድልድይ በግብረኃይሉ ሠራዊትና በመንገድ ባለሥልጣን እንደተሠራ ፣ ከዚያም የግብረ ኃይሉ መኖርያ ካንፕን ሲጐበኙ በየሔዱበት ቦታ ሁሉ አጽማቸውን ለአገር የከሰከሱ ፣ ወገኖቻችንን በማሰብ የሕሊና ጸሎት አድርገዋል ።

ሠራዊቱም በብፁዕነታቸው ጉብኝት ክርስቲያናዊ ሕይወቱ የመንፈስ ደስታን እንዳገኘ ከብፁዕነታቸው በተሰጠው ገለጻ ለመረዳት ተችሏል ።

### አርሲ

በአርሲ ሀገረ ስብከት 260 አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ ሲሆን የ16 አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤ የሥራ መነሻና መድረሻ ተመርምሮ የ16ቱም ሰበካ ጉባኤ ገቢ ብር 147.206.02 ከወጪ ቀሪ 490.38ብር የተገኘ መሆኑንና በዕዳ የሚፈለግ ብር 3.624.10 መሆኑን የሀገረ ስብከቱ ተቆጣጣሪ አስረድተዋል። ተቆጣጣሪው ያልተመረመሩት 244 አብያተ ክርስቲያናት በአስቸኳይ ቢመረመሩ ከዚህ የበለጠ ጉድለት እንደሚገኝ ጠቁሞ በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን በአንዳንድ ራስ ወዳዶች እንዳትራቆት አስቀድሞ መጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ለሚመለከተው ሪፖርት አድርጓል ።

## የዓለም አብያተ ክርስቲያን ዜና

### የእንግሊዝ ቤ/ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ጡረታ እንደሚወጡ አስታወቁ

ሎንዶን፡- የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ ዶክተር ዶናልድ ኮጋን በሚቀጥለው የአውሮፓውያን ዓመት ጥር 26 ቀን ሥራቸውን አስረክበው ጡረታ እንደሚወጡ ገለጡ ። ሊቀ ጳጳሱ በሚቀጥለው ዓመት የ70 ዓመት ሽማግሌ ይሆናሉ ። ሰባ ዓመትም ለእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ሁሉ የተወሰነ የጡረታ ዕድሜ ሆኗል ። ዶክተር ኮጋን በመንበረ ሊቀ ጵጵስና ለ4 ዓመታት ቤተ ክርስቲያናቸውን መርተዋል ። ሲል ኤክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ ሰኔ 7 ቀን 1979 ዓ.ም. (እ.ኤ) ባወጣው በቁ.15 46ኛ ዓመት እትሙ ገለጠ ።

### የጀርመኑ ጳጳስ ስለ ፍችና ጽንስ ማስወረድ አስጠነቀቁ

ሀኖቨር ፡- ጳጳስ ዲ. ኤድዋርድ ሎሀስ በየጊዜው ስለሚፈርሰው ጋብቻ በዚህም ምክንያት ስለሚበተኑ ቤተሰቦችና ከጋብቻ ስለሚርቁ ወጣቶች ጥልቅ ስሜት ያለበት ማሳሰቢያ ባለፈው ግንቦት ወር ሰጡ ። ጳጳሱ በመልእክታቸው ውስጥ፡- ‘‘ጋብቻ ምንም እንኳ ለማንኛውም ኅብረተሰብ የሚገባ ቢሆንም ክርስቲያኖች ጋብቻን እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝና ሕግ አድርገው ሊቀበሉት ይገባል’’ ብለዋል። የፅንስ ማስወረዱ ቁጥር እየጨመረ መሄዱንም አስመልክተው ጳጳሱ ተቃውሞአቸውን ገልጠዋል ።

ኤል ደብልዩ ኤፍ ኢንፎርሜሽን ግንቦት 30 1979 እ.ኤ.




www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዐምድ

## የጋብቻ አማካሪነት ትምህርታዊ ሴሚናር በሴራልዮን ዋና ከተማ በፍሪታውን ተካሄደ

እንደ ኤሮፖ አቆጣጠር ከሰኔ 2 -15 ቀን 1979 ዓ. ም በአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት አዘጋጅነትና በሴሪያሎን አብያተ ክርስቲያናት ተባባሪነት በፍሪታውን ከተማ ከመላ የአፍሪካ አገሮች ከሃያ አራት አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ 35 አባላት የተገኙበት የሁለት ሳምንታት ሴሚናር ተካሂዷል። የስብሰባው መሪ በአፍሪካ አ/ ክርስቲያናት ማኅበር በቤተ ክርስቲያን ም/የቤተሰብና ኅብረተሰብ ክፍል ዋና ጸሐፊት ወ/ት አይሳ ቢላ ጆንስተንና የአ. አብያ ክርስቲያናት ም/ፕሬዚዳንት ወ/ሮ አስቴር ኮከር ናቸው ።



ወ/ሮ አስቴር ኮከር ከአፍሪካ አ ክርስቲያናት ም/ፕሬዝዳንቶች አንድዋ

የሴሚናሩም ዓላማ 1ኛ/ ስለ ፍቅርና ጋብቻ ጠለቅ ያለ ጥናት ለመስጠት

2ኛ/ በቤተሰብ መምሪያ ለወደፊቱ በጋብቻ አማካሪነት ለሚሠማሩት መሠረተ ሃሳቦችንና ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ

3ኛ/ በቤተሰብ መምሪያ አማካሪነት የሙያ ትምህርት ለመስጠት ሲሆን፣ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አርእስት ለአፍሪካ-ውያት ሴቶች የክርስቲያን አባላት ኤሳሳቢነት ሴሚናሩ እንዲነጋገርባቸው የተደረገበት ዋና ምክንያት በቤተሰብ መካከል እየጨመረ ስለሚሄደው መለያየት፣ የጋብቻ አማካሪ ያለመኖር ስለሚያስከትለው ጉዳት ስለ ቤቱና ቤተሰብ ኑሮ ጉዳይ በፕሮግራም በመመራት ፣ ቤተ ክርስቲያንና አገር የሚበለጽጉበትን መንገድ ለመቀየስ ነው።

ሴሚናሩን በንግግር የከፈቱት በሴሪያሎን የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ዋና ኃላፊ የሆኑት ወ/ሮ ሮዝላይን እ.ፎርዴ ናቸው።

የመክፈቻው በዓል የተከበረው የአብያተ ክርስቲያናት አባላት፣ የክርስቲያን ድርጅቶች በሃገሪቱ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተወካዮችና ኃላፊዎች እንዲሁም ከየህብረተሰቡ የተውጣጡ ነዋሪዎች በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ነበር።

ስብሰባው የተካሄደው ከአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ም/ፕሬዚዳንቶች ከሆኑት አንዷ በወ/ሮ አስቴር ኩከርና በፎራ ኮሌጅ መምህርት በሆኑት በዶክተር ጁዲዝ ሜይ ፓርከር ሲሆን የሴሪያሎን ዩኒቨርሲቲም በ ቤተሰብ እና ኗር ርእስ ላይ ጠቃሚና በአንድ ህብረተሰብ ሊኖር ስለሚገባው ሕይወት በመተንተን ገለጻ አድርገዋል።

በአሜሪካ አገር ከሚገኘው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎትም በሰሚናሩ ለሚገኙ የስብሰባው ተካፋዮች የደስታ መግለጫ በሚስስ ኢሉሚንዳ ሮሪኩዝ ሲልክ በቤትና ቤተሰብ ኑሮ ኮሚቴ ሊቀ መንበር በሆኑት በሚስስ አሚ ፓት አማካኝነት ሞቅ ያለ አቀባበል ከምስጋና ጋር ተደርጎላቸዋል።

በስብሰባው ላይ ከ35ቱ የስብሰባው ተካፋዮች የተዘጋጀ ስለቤተሰብ መምሪያና የጋብቻ አመራር ሁኔታ የተዘጋጀ ልዩ ልዩ ጽሑፎችና ስዕሎች ነበሩ።

ከዚህም ሌላ በሴሚናሩ ላይ ለተሰጠው ትምህርት ተባባሪነት የሆኑት ሚስተር ደቪድ ዳርቲ ከጋና አብያተ ክርስቲያናት፣ ዶክተር ቴድ ስቶንበርግ ከኬንያ ብሔራዊ የክርስቲያን ምክር ቤት ቀሲስ ለሴ ሺሎን ከፎራ በይ ኮሌጅ የሴሪያሎን ዩኒቨርስቲ፣ ሚስተር አለንሻው ከሴሪያሎን ዩኒቨርስቲና ሚስተር ጆን ባንዩክ የጋብቻ መምሪያ አማካሪ ያውንዴ ካሜሩን ናቸው።

ከሰኔ 11-14 /1979 ዓ.ም የነበረው አጀንዳ በተራ ቁጥር 3. የተጠቀሰው በቤተ ሰብ መምሪያ አማካሪነት የሙያ ትምህርት መስጠት ነበር።

በዚህ ሰዓት ተካፋዮቹ ጋብቻን በሚመለከት ረገድ ብዙ ጥናት ያካሄዱ ከመሆናቸውም በላይ ስለ ጠቅላላ የጋብቻ መሠረተ ሐሳቦች፣ ስለ አጠባበቅ ሥራና ፕሮግራም አመጣጥ፣ ዳግመኛ ትዳር ስለመመሥረትና የቤተሰብ ኑሮ ፕሮግራም ጠለቅ ያለ ዕውቀት ገብይተዋል።

ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ስለሚያደርጉት ተሳትፎ ግለትም እንደ የዓለም የጸሎት ቀንና የመጨረሻ ሳንቲም የመሰብሰብ ማኅበሩ ውይይት ተደርጐበታል ። ቀደም ብለው በተላለፉት መጠይቆች አማካኝነትም ተወካዮች በበኩላቸው ከሃገራቸው ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር የየግላቸውን አስተያየትና መልስ ሰጥተዋል ።

በየአጀንዳው ላይም ቡድን በቡድን በመከፋፈል ተግባራዊ የሆነ ውይይት ተካሂደዋል የስብሰባው ተካፋዮች በግለሰቦችና በሴሪያሎን የሴቶች የቤተ ክርስቲያን ማኅበር አባላት ከፍተኛ አቀባበል የተደረገላቸው ከመሆኑም በላይ



ወ/ት አይሳቢላ ጆንስተን

ባሕር ዳር አካበቢ በሚገኙ ገጠሮች አካባቢ የምሳ ግብዣ አድርገውላቸዋል። በዋናው ከተማም ጉብኝትና በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መጸለይ የስብሰባው አባላት ከሥራዎቻቸው ጥቂቶቹ ነበሩ በመክፈቻው ዕለት ጸሎት የተደረገው ፍሪታውን ከተማ በሚገኘው በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ነበር።

የተባበረው የሴሪያሎን የክርስቲያን ምክር ቤት የሴሚናሩን ዝግጅት ምክንያት በማድረግ ብሩክ ፊልድ በሚገኘው የወጣት ሴቶች ክርስቲያናዊ ማህበር ዋና መሥሪያ ቤቱ ሕንፃ የመሰነባበቻ ግብዣ አድርጐላቸዋል።

በስብሰባው ፍጻሜ ቀንም ትምህርቱንና ስብሰባውን ለተካፈሉ ሁሉ በአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ም/ፕሬዚዳንቶች ከሆኑት አንዷ በወ/ሮ አስቴር ኩከር እጅ የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል። በመጨረሻም ከየሀገሩ ተወክለው የመጡት ተወካዮች በመተባበር የቤተሰብ ኑሮ መገንባት የሚቻልበትን ከፍተኛ ዕውቀትና አጥጋቢ የሆነ ትምህርት ለመቅሰም ያበቃቸውን የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርንና የአስተናጋጁን ኮሚቴ ከልብ አመስግነዋል።

ከኢትዮ.ኦ.ተ.ቤ/ክ. የጉባኤው ተካፋይ

ወ/ት ብርሃን ተድላ



# አስተያየት—ከያሬድ አስቻለው

በቁጥር 21 ትንሣኤ መጽሔት
በአቶ ደምሴ በቀለ ለተጠየቀው
ጥያቄ ምእመናን በተሰነዘረው ሃሳብ
እርምጃ እንዲወስዱበት
አሥራት በኩራት
ለእግዚአብሔር አንሰጥም?
ከአሥር እጅ ገቢያችን

አንድ እጁን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥተን በረሃብ ፣በድርቅ በጦርነት ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን እንዲረዱበት አናደርግም?

አቶ ደምሴ በቀለ ከአዋሳ የጠየቁትን ጥያቄ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የትንሣኤ መጽሔት አንባብያን ሐሳብ ሳይሰጡበትና አስተያየቱ በግብር እንዲተረጐም ካልተደረገ የመጽሔቱ መልእክት ዋጋ እንዳያጣ እፈራለሁ

እኔ ግን የበኩሌን አሥራት በኩራቱን አውጡ ህሙማንና የታሠሩን ጠይቁ፣ ችግረኞችንና ስደተኞችን ጐብኙ የሚለውን ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ ማክበር እንዲቻለን አሥራት በኩራት ለቤተ ክርስቲያን መስጠት ይኖርብናል።

1ኛ/ ምሳሌ ም. 21 /ቁ.9/ ርህሩህ የተባረከ ይሆናል ከእንጀራው ለድሀ ሰጥቶአልና

2ኛ/ ምሳሌ ም. 28 ቁ.27/ ለድሃ የሚሰጥ አያጣም አይኖቹን የሚጨፍን ግን እጅግ ይረገማል ሲል ጠቢቡ ሰሎሞን በነዚህ ተከታታይ ምዕራፎች በሰጠው የጥበብ ትምህርቱ ርህሩህ የተባረከ እንደሚሆን፣ የሚሰጥም እንደማያጣ፣ የሚከለክል ግን እንደሚረገም ያስታወቀ ስለሆነ፣ እንድንባረክ እንዳናጣ፣ እንዳንረገም ለቤተ ክርስትያን የሚገባውን አሥራት እናዋጣ።

ፈጣሪያችን ብዙ ሰጥቶናል፣ እኛ ግን ከ10 አንድ ከልክለናል። በዚህም በረከቱን እንዳናጣ ብንሞክር ይሻላል።

ሁሉን በነፃ ለሰጠ ጌታ ከአሥር አንድ ለቤተ ክርስቲያኑ አንሰጥም?

ቤተ ክርስቲያን ፀንታ እንድትቆይ ልጆቿ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲቀርቡ መጠናከር ይኖርባታል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላም የሚጠፋው ም



አስተያየቱን ያቀረበልን ያሬድ አስቻለው

ዕመናን መምህር ሲያጡ ነው መምህራን በቤተ እግዚአብሔር በብዛት የሚታጡት ምዕመናን አሥራት በኩራት የቤተ ክርስቲያን ገቢ የካህናት ደምወዝ በወቅቱ ሳያገቡ ሲቀሩ ብቻ ነው።

አቶ ደምሴ በቀለ በሰጡት አስተያየት አማንያን አሥራት ከማውጣት ይልቅ ድግስ ደግሶ ማብላትን ይመርጣሉ። አብዛኛዎቹ ሃይማኖታቸውን ለማክበር ሳይሆን፣ በሞቱ ጊዜ ጸሎተ ፍትሐት እንዲደርስላቸው፣ ልጅ በወለዱ ጊዜም ክርስትና እንዲያስነሱ አራት ብር ብቻ ይሰጣሉ።

ያሉትን በንባብ ብቻ ተመልከተን የምናልፈው መሆን የለበትም። ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ እናት ቤተ ክርስቲያናችን እንደምን ሆኖ በሙታን የፍትሃት መዋጮና በክርስትና አራት ብር ብቻ አሥራት ከልጆቿ አጥታ የካህናቱ የወር ገቢ $40.—ብር የማደሪያ ሥፍራቸው በየመቃብሩ ቤት ቀለባቸው በየደጀ ሰላሙና በየሰንበቴ ቤቱ ሁኖ እምነታችንን እናስፋፋለን? የምንለው እንደምንስ ሆኖ ለሕዝብ የተሰጠችው ቤተ ክርስቲያን ያለአሥራት መዋጮ መጠናከርና መሻሻል ይቻላታል ተብሎ ይገመታል?

ሌሎች እንኳን ገንዘባቸውን ሕይወታቸውን እስከመስጠት ሞቅ ያለ መንፈስ ሲታይባቸው ምነው እኛ ለሚለው የአቶ ደምሴ በቀለ ሃሳብ የተዋህዶ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አማንያን የሆን ሁሉ በየሰበካው ጉባኤ በኩል ምዕመናኑ አሥራት እንደአያት ቅድመ አያትህ ለቤተ ክርስቲያንህ አምጣ ቢባል የጧፍና የሻማ ክምር የወርቅና የብር ዣንጥላዎች የሚያግዘው ምዕመን አሥራት እምቢ አይልም ።

እኔም እንደ አቶ ደምሴ እንዳየሁት፣ ምእመናን የሚሉት አስተምሩን ነው። አስረዱን ነው ሃይማኖታችንን አስጠኑን ነው የሚሉት።

ይህንም ሲሉ ከአመት እስከአመት ሱቲ በማንጠፍ፣ ዣንጥላ በመወጠር የጻድቃንን የመላእክታትንና የሰማዕታትን ስዕል በመያዝ አሮጌ ካርኒ በማዘጋጀት ሁል ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ እርዱን እያሉ አንድ ቀን ኑ አስቀድሱባት ሳይሉን ብራችንን እየያዙ ጭልጥ በሚል አርቲፊሻል ባህታዊ ነን ባይ ወስላቶች አታዘርፉን ነው የሚሉት እና በዚህም በኩል ይታሰብበት።





www.ethiopianorthodox.org

# ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች

## ሂዱና አስተምሩ

ክርስቶስ ሒዱና አስተምሩ ባለው መሠረት ሐዋርያት ይህን መመሪያ በማድረግ በየገጠሩ በየዳርቻው እየተዘዋወሩ ተረስተው የነበሩትን ሕዝቦች ሁሉ ማስተማራቸውን በቁጥር 16ና 17 ትንሣኤ መጽሔት መግለጻችን ይታወሳል፤

አሁን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በተረሱ ሕዝቦች ፊት «ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው»ሲል ክርስቶስ መረጠው ስለዚህ ዐዋቂ ነን በሚሉት በእሥራኤል መካከል እየዞረ ከማስተማር ይልቅ ወደ ተረሱ ሕዝቦች እየዞረ ማስተማርን መረጠ ፤ በየገጠሩም እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ ከብዮኢቸው የነበረው የጭቆና ዘመን ማለፉንና የእኩልነት፡ የሰላም፡ የፍትሕ ፤ ዘመን መምጣቱን ሰበከላቸው።

ለምሳሌ አንድ ቤት ካረጀ በኋላ በየጊዜው ቢጠግኑት ስላረጀ ጉልበትን ከማድከምና ገንዘብን ከመጨረስ በቀር ጥቅም አይሰጥም ነገር ግን በፍጹም አፍርሶ ከፍራሹ ያልነቀዘውንና ያልተጣመመውን እንጨት ጨምሮ አዲስ ቤት መሥራት እንደሚያስፈልገው ግልጽ ነው ይህም ሲተነተን አሮጌው ሥርዓት ፈርሶ ፣የጭቆናው ዘመን አልፎ በምትኩ አዲስ የሰላም ፡ የነፃነት፡ የእኩልነት ፤ በኅብረት ሠርቶ አብሮ የማደግ አዲስ ሥርዓት መተካቱን በትምህርቱ እንደገለጸላቸው ያስገነዝበናል።

ይህንን መሠረት በማድረግ ሐዋርያው በየገጠሩ እየተዘዋወረ የተረሱ ሕዝቦችን ሲያስተምር በክርስቶስ ዘንድ ባለጠጋና ድሃ ፤ ወንድና ሴት ፤ አሽከርና ጌታ ፤ እመቤትና ገረድ ትክክል ናቸው እንጂ አንዱ ከአንዱ አይበልጥም ብሏል ሮሜ 10 ፥12 ነገር ግን ልዩነት ያለ በሚሠራና በማይሠራ በኃጢያተኛና በጻድቅ መካከል ነውብሎ ስላስተማረ ትምህርቱን በደስታ ተቀብለው ሁሉም ወደ ሥራው ዓለም ተሠማሩ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት በዚያን ዘመን የነበሩ ሠራተኞች ሥራን ከመሥራት የሚለግሙት የድካማቸውን ዋጋ በትክክል ባለማግኘታቸው ነበር።

የተረሱ ሕዝቦችም አገራቸው የምትሰጠውን በረከት ለመካፈል ካለመቻላቸውም ሌላ በማይምነት ተውጠው ፣ ከዕውቀት ርቀው ፤ በጭለማ ውስጥ ይኖሩ ነበር ስለዚህም ሰዎችን በሥራአትለግሙ ያልሠራ አይብላ ሲል በማስተማሩ አሠሪዎችም ሆኑ ሠራተኞች ትምህርቱን ተቀብለው ሥራቸውን በህብረት ከመሥራታቸው የተነሣ ሁሉም የዕውቀቱም የጥቅሙም ተካፋዮች ስለሆኑ ለሀገራቸው ታላቅ ዕድገት ሰጡ። ሥራንም ለማጠናከር ሲያስተምር እርሻው የጣፈጠ ከሆነ ዳቦውም የጣፈጠ ይሆናል አንድ ዛፍ ጣፋጭ ከሆነ ፍሬው ሁሉ ጣፋጭ ይሆናል እያለ ሰዎች የሥራ ፍቅር እንዲያድርባቸውና ወደ ሥራው ዓለምም እንዲሳቡ አድርጓል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሐዋርያው በተረሱ ህዝቦች መካከል ተገኝቶ ተግቶ ባለመሥራት ምርት እንደሚቀንስና ተግቶ በመሥራትም ምርት እንደሚበረከት ሲስተምር «በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከተ ያጭዳል» እግዚአብሄር በደስታ የሚሠራውንናየሚሰጠውን ይወዳልና ብሏል

ጳውሎስ በዚህ ብቻ ሳይወሰን በተሰሎንቄ ላሉ ለተረሱ ሕዝቦች በሁለተኛው መልእክቱም 3 ቁጥ 8 ከሁሉ አስቀድሞ ወንድማማችነትንና ፍቅርን፡ እንዲሁ ደግሞ ሠርቶ መኖርን ፡ ሲያስተምር «ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካም በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም» በማለት የሥራን ክቡርነት ገልጾአል ።

በተጨማሪም ስለ ክርስቶስ ወንጌል ሲያስተምር አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ለሚያምኑም ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና በማለት መንፈሳዊ ሕይወታቸው ለጨለመባቸውና ኑሮአቸው ለተጐሳቈለባቸው ለተረሱ ሕዝቦች በሮም ተገኝቶ ይህን አብራርቶላቸዋል ስለደህንነትም ሲናገር በክርስቶስ የሚሰጠው ደህንነት ለሰው ሁሉ መሆኑን በሰፊው ገልጿል።

እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ በተረሱ ሕዝቦች መካከል እየተገኘ እንዳስተማረና ጥሪውንም አክብሮ አገልግሎት እንደሰጠ ተመልክተናል ። ዛሬም ቤተክርስቲያናችን በተረሱ ሕዝቦች መካከል እየተገኘን መሀይምነትን ለማጥፋት እንድንዘምት መምህራንና ካህናት የሆነውን ሁሉ ሂዱና አስተምሩ እያለች በየጊዜው ትጠራናለች ቤተ ክርስቲያንም የምትጠራን በምቾት ተቀምጠን ሌሎችን እንድናዝና እንድናስተዳድር ሳይሆን ለአገልግሎት ልትመድበን መሆኑን በመጀመሪያ ማወቅ አለብን።

ለምሳሌ ዮናስ በነነዌ ከተማ የተረሱ ሕዝቦችን እንዲያስተምር ከእግዚአብሔር ጥሪ ደርሶት ነበር እሱ ግን የማስተማሩን ጉዳይ ሌሎች ይጨነቁበት ሲል ራሱን ለማዝናናት ወደ ሌላ ሥፍራ እንደኮበለለ ታላቁ መጽሐፍ ይነግረናል ቤተ ክርስቲያንም እንዲህ ያሉትን መምህራንና ካህናት ታጋልጣቸዋለች እንጂ በአርምሞ አትመለከታቸውም በዮናስም የተፈጸመው ተግሳጽ እንደሚደርስባቸው እሙን ነው እንደ ቅዱስ ጳውሎስ በየገጠሩ እየተዘዋወሩና በተረሱ ሕዝቦች መካከል እየተገኙ መሀይምነትን ከኢትዮጵያ ምድረ ገጽ የሚያጠፉ ንቃተ ህሊና እየሰጡ የሚተስቱና የሚያስተምሩ ብዙ ጳውሎሶችን ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ በመብራት ትፈልጋለች።

በኢትዮጵያ 18ሺህ አብያተ ክርስቲያናትና 200.000 በላይ ካህናት እንደሚገኙ ይገመታል እነዚህ ሁሉ የመሠረተ ትምህርት ተባባሪ ሁነው ማይምነትን ለማጥፋት ዘመቻ እንዲያደርጉ ቤተክርስቲያናችን ጥሪዋን ታስተላልፋለች ከላይ የተጠቀሱትም ካህናት ማይምነትን ለማጥፋት በሚደረገው ዘመቻ ተካፋይ በመሆን በየገጠሩ እየተዘዋወሩና በተረሱት ሕዝቦች መካከል እየተገኙ በየዛፉ ሥር፡ በየሰንበቴው ቤት፡ በመቃብር ቤት፡ በደጀ ሰላም፡ማይሞችን እየሰበሰቡ እንዲያስተምሩ አደራ ተጥሎባቸዋል።

አባቶች ሲመስሉ «ለሰዎች የማያካፍሉት ትምህርት በጉድጓድ ውስጥ እንደተቀበረ ወርቅ ነው» ይላሉ አባባሉ መልካም ነው እኔ ከፃፍኩና ካነበብኩ፡ እኔ ካወቅሁ ሌላው ባይጽፍና ባያነብ፡ ባያውቅ ምንችገረኝ የምንል ከሆነ ትምህርታችን ሁሉ ለሌላው የማያሳይ የጋን መብራት ይሆናል ማለት ነው ይህ እንዳይሆን ሁሉ ይማር ፡ ሁሉ ያስተምር የተባለው ቃል በተግባር ላይ እንዲውል ማይምነትን ለማጥፋት ከሚደረገው ዘመቻ ሁላችንም ተባባሪ እንድንሆን ይፈለግብናል ሂዱና አስተምሩ የሚል አምላካዊ ትእዛዝ አለና።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



## ሊቃውንቶቻችን

ከገጽ ፲፰ የዞረ

መውለድ መመረጥዋን ፤ ንጽሕናዋን ቅድስናዋን ርኅራኄዋን ለሰው ልጆች ያደረገችውንና የምታደርገውን በጐ ተግባር ፤ እንዲሁም የአምላክን ሦስትነትና አንድነት የመሳሰሉትን የሚያመለክቱ ናቸው ።

ከዚህም ጋር ሰው ካልሠራ በሥጋውም ሆነ በነፍሱ የ ማይጠቀም መሆኑን የሚያረጋግጡ ተግባራውያን መፈክሮች መሆናቸው ታውቋል ። መጽሐፈ ምሥጢርም በዓለም ያለውን የሃይማኖት ልዩነት በዝርዝር የሚያስረዳ በመሆኑ ከፍተኛ ውጤት ያለው ነው ።

በአንድ ዓመት ውስጥ በሚገኙት ሦስት መቶ ስድሣ አምስቱ ዕለታት መጠን ስንክሣርን በመከተልና በዓላቱን በማስመልከት የደረሱት እግዚአብሔር ነግሡ የድርሰት ሰው መሆናቸውን አጉልቶ ያሳያል ።

አባ ጊዮርጊስን የሚያስመሰግናቸው የታሪክና የሥራ ሰው የሚያደርጋቸው ከትምህርት ሊቅነታቸው ጋር የድርሰት ሰው መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሥነ ጽሑፋቸው በጥራቱ ፤ በምጥቀቱና በጥልቀቱ ሲለካ ሚዛናዊ በመሆኑም ጭምር ነው ።

አባ ጊዮርጊስ ሁለተኛው ያሬድ ናቸው

የቅዱሳት መጻሕፍት ምርምርና የድርሰት ቅንብር ሙያ ከዜማ ስልት ችሎታ ጋር ተስማምቶ የተሰጣቸው አባ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ድቀ መዛሙርት ከአስተማሩዋቸው ከአባ ጌራ ዘንድ ወሎ ሐይቅ አጠገብ ከሚገኘውና ደብረ እግዚአብሔር ከሚባለው ቦታ ሆዋትወ ዜማን በሙሉ ተምረዋል በበኩላቸውም ብዙዎችን ደቀ መዛሙርት አስተምረዋል ።

ከዜማ ደቀ መዛሙርቶቻቸውም መካከል ልሳነ ዕፍረት መራሂ ዘቤተ ልሔም የተባለው ስመ ጥሩ ሊቅ ይገኝበታል ።

አባ ጊዮርጊስ በዜማ ማስተማር ብቻ ሳይወሰኑ እንደ ደቀ መዛሙርቱ ፍላጐት በአጠቃላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያስተምሩ እንደነበረ ይነገርላቸዋል ።

የዕረፍታቸው ዜና

ሞት ፤ ታታሪ ሠራተኛም ሰነፍም የሚጓዝበት ጥርጊያ መንገድ ስለሆነ ብዙዎቹ ሊቃውንት በመቶና ከዚያም በላይ ባለው ዕድሜያቸው ሊሠሩ ያልቻሉትን ልዩ ልዩ ታሪካዊና መንፈሳዊ ተግባር በ60 ዘመን ዕድሜያቸው ብቻ አከናውነው ሐምሌ 7 1417 ዓ. ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገልደትና የሞት ቀናቸው አንድ በመሆኑ ይህንን የሚያነቡ ሁሉ ምን ያህል ይደነቁ ይሆን?

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

## ለቤተ ክርስቲያን …

ከገጽ ፲፯ የዞረ

መንገድ ጠባብ ነው ። ይህም በመሆኑ በሶሺያሊስት ሀገሮች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ያለ ቅራኔ በነፃነት ትኖራለች ። የኅብረተ ሰቡንም የኑሮ እድገት በሚመለከት ጉዳይ ከመንግሥት ጋር በመተባበር የሥራ ተሳትፎዋን ታሳያለች በሀገራችን በኢትዮጵያም ኅብረተ ሰብአዊነት ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን እምነትዋን እንዳታስፋፋ ወንጌልን እንዳትሰብክ አንዳች ተጽእኖ ሳይደርስባት በሙሉ ነፃነትና መብት ትገኛለች ስለ ሀገር ብልጽግናና ስለ ኅብረተሰቡ የኑሮ መሻሻል መንግሥት በሚያወጣቸው ፕሮግራሞች ሁሉ ትብብርዋን ታሳያለች ኅብረተ ሰብአዊነትንም የጐሪጥ አታየውም ወደ ኋላም አትቀርም ። ግን እምነትዋን ጠብቃ ከኅብረተ ሰቡ ጋር ትራመዳለች ።

### ምስጋና

በዚህ እትም ላይ «ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ» በሚለው ርእስ የወጡትን ጥንታውያን ፎቶግራፎች የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ስለ ፈቀደልን ወደፊትም ትብብሩ እንደማይለየን ሙሉ ተስፋ ስለሰጠን እጅግ እናመሰግናለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ

የሉቃስ ወንጌል ። ምዕራፍ ፩

፴፱-፵፭ ማርያም ኤልሳቤጥን እንደ ጐበኘች
፴፱ ማርያምም በዚያ ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው
አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች ፤ ፵ ወደ ዘካርያስም ቤት
ገብታ ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት ። ፵፩ ኤልሳቤጥም የማርያምን
ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ ፤ በኤልሳ
ቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት ፤ ፵፪ በታላቅ ድምፅም ጮኻ እን
ዲህ አለች ፦ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ ፤ የማኅፀ
ንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ። ፵፫ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ
ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል ? ፵፬ እነሆ ፤ የሰላምታሽ ድምፅ
በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና ።
፵፭ ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት ።




የጌታዬ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም
ሆይ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ

የድንግል ማርያም የምስጋና (መዝሙር) ጸሎት
፵፮ ማርያምም እንዲህ አለች ፦
ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች ፤ ፵፯ መንፈሴም በአምላኬ
በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች ፤ ፵፰ የባሪያይቱን ውር
ደት ተመልክቶአልና ። እነሆም ፤ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ
ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ፤ ፵፱ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ
ሥራ አድርጎአልና ፤ ስሙም ቅዱስ ነው ። ፶ ምሕረቱም
ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል ። ፶፩ በክንዱ
ኃይል አድርጎአል ፤ ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በት
ኖአል ፤ ፶፪ ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዶአል ፤ ፶፫ ትሑ
ታንንም ከፍ አድርጎአል ፤ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግ
ቦአል ፤ ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል ። ፶፬-፶፭
ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ ፤ ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም
ምሕረቱ ትዝ እያለው እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶ
አል ።
፶፮ ማርያምም ሦስት ወር የሚያህል በእርስዋ ዘንድ ተቀመጠች
ወደ ቤትዋም ተመለሰች ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
ፖስታ ሣጥን ቍጥር 30755
አዲስ አበባ ።



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ስመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org